# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የቲዎሪ መዕሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## ቋንቋና አብዮታዊ ትግል

## ቋንቋዎች በኢትዮጵያ


የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

የካቲት 1964

## ድንቋና ሬቮሉሽናዊ ትግል ::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበሮች በውጭ አገር የ
ሚያወጧቸውን መጽሄቶች በገት ሰው ያነባቸዋል::ይህ ጥ
ያቄ ተመላልሶ ይቀርብልናል::አንዳንድ ሰዎች እንዲያው
ም እነታጠቁ፣ትግላችን፣ቻሌንጅን ማውጣት የጉልበት : የ
ጊዜና የገንዘብ ማባከና ነው እንጂ ሌላ ፋይዳ የለውም
እያሉ ብዙ ጊዜ ተስፋ ሊያስቆርጡንና ትግላችንን ሊያስ
ጥሉን ይሞክራሉ:: "በኢትዮጵያ ማንበብና መጻፍ የሚያው
ቅ ሰው ከሕዝቡ ቢበዛ አሥር በመቶ ቢሆን ነው:ከዚህ
ከሚያነቡት ክፍል ደግሞ አንድ አሥረኛው እንኳን መጽሄ
ቶቻችሁን አያገኝም:የምትለፉት በከንቱ ነው:የምትገባው
ት በባዶ ቦታ ነው" ይላሉ::የዚህ አስተያየት አውነ
ተኛነት አስከፊን ደረሰ ነው::

እርግጥ ነው:በቁጥር በኩል ከሄድን መጽሄቶቻች
ንን የሚያነቡ በጣም ጥቂቶች ናቸው::ካገሪቱ የሕዝብ
ብዛት ጋር ሲመባሰሉ በቁጥር አይገቡም::ነገርግን ሬቮ
ሉሽናዊ አስተያየት እንደሰደድ እሳት ነው:.በመጀመሪያ
የሚታየው ትንሽ ፍንጣሪ ነው:ትንሽ ብልጭታ ::ይህች
ፍንጣሪ ያቀጣጠለችው እሳት እየሰፋ ይሄዳል::ካንድ ደ
ረጃ ላይ ቢደርስም ከነበልባሉ ፊት ሊቆም የሚችል ሀይ
ል አይኖርም::

አሁን ባለንበት ደረጃ ነገሩ የቁጥር ጉዳይ ሳ
ይሆን የዓይነት ጉዳይ የሚሆነው ይህ ዲያሌክቲካዊ አስ

ተዳደግ ስላለ ነው::ዛሬ በትግሉ የተጀመረው አንድ ቀ
ን መላ ኢትዮጵያን እንደሚያጥለቀለቃት እርግጠኛ ነን::
ስለዚህም ተግባራችን በያዝነው መንገድ ያለመታከት መግ
ፋት: መጽሄቶቻችንን በአይነትም ሆነ በቁጥር ለማዳበር
መታገል መሆኑ ለማንም ጊዜ: ለማንኛውም አንባቢ: ግልጽ
መሆን አለበት::

ስለመጽሄት ጥቅም ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ተደጋግ
ሞ ተነግሮአል::መጽሄት ያስተምራል: መጽሄት ይሰበስባል:
መጽሄት ያደራጃል::ይህ የማይካድ ሀቅ ነው:: ይህ ከ
ሆነ የጊዜው ዋና ጥያቄ ለማስተማር: ለመሰብሰብና ለማ
ደራጀት የምንፈልገው የትኛውን የህዝብ ክፍል ነው የሚ
ለው ይሆናል::ለጊዜው ጽሁፎቻችን የሚደርሱት ለጥቂቶች
ተማሪዎች: አስተማሪዎችና የቢሮ ሰራተኞች ብቻ ነው::
ማለት በየከተማው ለሚገኘው ለትንሽ ከበርቴ መደብ::
አንዳንዶም በጠበታ በገጠር ለሚኖሩት ለዚሁ መደብ አባ
ሎች ይደርሳል::ከዚያም በጣም በተወሰነ መጠን የትግላች
ን ዜና ተንጠባጥቦ ለሰራተኛውና ለገበሬው ይደርሳል::
ይሁን እንጂ አሁን ባለንበት ደረጃ ከዚህ የተሻለ ውጤት
ለማግኘት መቻል አለብን ብለን እንገምታለን::

ባሁኑ ጊዜ የተማሪ እንቅስቃሴአችን ያለበት ሁ
ኔታ ቅራኔን ይዘአል::ባንዱ በኩል የኢትዮጵያ ህዝቦች
ትግል በስፋትና በጥልቀት በየእለቱ እየጨመረ ይሄዳል::
ለዚህ የኤርትራን: የባሌ አሩሲን: የውጋዴን ህዝቦች
ትግል ማስታወስ ይበቃል::በሌላ በኩል ግን እኛ ረቦሉ



ሽናዊ ርእዮተ አለምን ለማስራጨት የምንፈልግ ተማሪዎች
ከሚታገሉት ህዝቦች ጋር ያለን ግንኙነት እጅግ በጣም
የተወሰነ ነው::በውጭ አገር ያለነው ብቻ ሳንሆን ባገ
ር ቤትም የሚገኙት ጓደቻችን ከሰርቶ አደሩ ህዝብ ጋር
ያላቸው ግንኙነት እንደዚሁ የተወሰነ ነው::ይህ ሁኔታ
የሚሻሻልበትን መንገድ ለማግኘት መጣጣር አለብን::ለዚ
ህም አንዳንድ ዘዴዎችን ለማቅረብ ይቻላል::

1ኛ/ የመጽሄት አንባቢዎቻችን ይዘቱን ለሰርቶ
አደር ህዝብ ለማድረስ መታገል አለባቸው::መጽሄት ሲያ
ገኙ አንብበው ላላነበበ ማስተላለፍ: ካጋጠማቸው ሰው
ጋር ይዘቱን መወያየት:ዋና ዋናዎቹን አሳቦች ላካባቢያቸ
ው ማስረዳት አለባቸው::2ኛ/ ትምህርታችንን ጨርሰን
ወዳገር ቤት ስንመለስ ከሰርቶ አደሩ ህዝብ ጋር የመቀ
ላቀሉን አሳብ መርሳት የለብንም::የመንግስትም ሆነ የ
ሌላ ስራ ይዞ በዚሁ ብቻ ተወስኖ መኖር እዚህ ሆነን
የነበረንን አላማ እንደአሮጌ ጨርቅ መወርወር ይሆንብና
ል::ባገር ቤት ውስጥ መንቀሳቀስ: የህዝቦችን ኑሮ ማወ
ቅ: የተቻለውን እርዳታ ሁሉ — ማቴሪያላዊም ሆነ ያስ
ተሳሰብ — ላካባቢው ሰርቶ አደር ማድረግ ያስፈልጋል::

ይህ ሁሉ ቀላል ነገር አይደለም::የማያቋርጥ
ትግልን ይጠይቃል::ግን ከሰፊው ህዝብ ጋር ግንኙነት
ለማድረግ በምንታገልበት ጊዜ ከፊታችን ሌሎች መሰናክሎ
ች ተደቅነው እናገኛለን::ከነዚህም አንዱ የቋንቋ መሰ
ናክል ነው::በእንግሊዝኛ የሚታተመውን ቻሌንጅን /አሁ
ን በቅርቡ ደግሞ ኦብዘርቨርን/ አንብበው በደንብ ሊረዱ

የሚችሉ የዩኒቨርሲቲ ተምህርት ያላቸው ብቻ መሆናቸውን ለመገመት ይቻላል፡፡እርሱን ወደጎን ትተን ያማርኛ ጽሁፎቻችንን እንኳን በንወስድ ብዙ ችግሮች አሉ፡፡1ኛ ከትግሉ ቦታ በመራቃችን የምንጽፈው ነገር ከጊዜው ጋር የሚሄድ ይሁን አይሁን ለማወቅ አንዳንዴ ያዳግተናል፡፡ 2ኛ፡የምንጠቀምበት አማርኛ ራሱ እንኳንስ ሰፊው ሕዝብ የሚናገረው ሊሆን፡እንዲያውም የከተማው ተራ አንባቢ የማይረዳው ሊሆን ይችላል፡፡3ኛ፡በኢትዮጵያ ብሄሮች ደረጃ እስከዛሬ ለኤርትራና ለባሌአሩሲ፡እንደዚሁም ለሌሎች ተዋጊዎች በየቋንቋቸው እንዳችም አስተዋጽኦ አላደረግንም፡፡...በኢትዮጵያ የሚገኘው ሬቮሉሽናዊ የሕዝብ ትግል ወደፊት እንዲራመድ ለማድረግ ከፈለግን እነዚህን መሰናክሎች ቶሎ ማሸነፍ አለብን፡፡

አንደኛውን ነጥብ በሚመለከተው በኩል፡በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ያሉት ሬቮሉሽናዊ ተማሪዎች፡በየቦታው የሚገኙት አንባቢዎቻችንና የትግላችን ደጋፊዎች ሁሉ በየጊዜው ጽሁፎችን እያዘጋጁ ቢልኩልን፡በዚህ አኳኋን መጽሄቶቻችንን መጽሄቶቻቸው ቢያደርጉዋቸው፡መጽሄቶቻችንም ሆነ የያዟቸውን ሐሳቦች በዙሪያቸው ቢያሠራጩ ችግሩ በርግጥ ይቃለላል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በሚመለከተው በኩል፡በምንጽፍበት ጊዜ የምንጠቀምበት ቋንቋ ቀላልና ለማንበብ ለሚችል ሰው ሁሉ የሚገባ እንዲሆን መጣጣር አለብን፡፡አንዱ ደራሲ ጥሩ አድርጎ እንደተናገረው ሁሉ፡ሬቮሉሽናዊ እውነት ከሰፊው ሕዝብ የእለት ኑሮ ጋር የተያያዘ ስለሆነ



ለርሱ የሚጨበጥ፡የሚዳሰስ ነው፡፡የኛ የምሁራን ተግባር ይህንን እውነት በቀላሉ ገልጠን የማሳየት ጉዳይ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ 'በመራቀቅ' ግልጽ የሆነውን ነገር በምሁራዊነት ጭጋግ ሸፋፍነን የማቀረብ መጥፎ ልምድ አለብን፡፡በዚህ ዓይነት ጽሁፋችን ከግቡ ሳይደርስ ይቀራል ስለዚህም በንጽፍ ትልቅ ጥንቃቄ ብናደርግ ሁለተኛው ችግር የሚቃለል ይሆናል፡፡

ሶስተኛው መሰናክል የበለጠ አስቸጋሪ ነው፡፡በብሄሮች ቋንቋዎች ጽሁፎችን ለማቀረብ አሁን ባለንበት ጊዜ ብዙ የጉልበትና የችሎታ ማነስ ወይንም እጦት አለብን፡፡ይሁን እንጂ በብዙዎቹ ቋንቋዎች የመጻፉ ነገር እንኳን ረዥም ያለ ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም፡በትግራይና በኦሮሞ ቋንቋዎች በቀርቡ ጽሁፎችን ማዘጋጀት መጀመር አለብን፡፡ከኤርትራ ሕዝብና ከባሌአሩሲ ሕዝብ ትግል መፋፋም የተነሣ፡ባሁኑጊዜ ሬቮሉሽናዊ አስተያየትን ለሕዝቡ የምናደርስበት ሁኔታ የተፈጠረ ይመስላል፡፡

ይህኛውን የታጠቀ ቁጥር ለቋንቋ ችግር ለማዋል ያሰብነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ለመጀመር ያህል፡ስለአማርኛና ስለኦሮምኛ ሁለት ጽሁፎች ቀርበዋል፡፡በመጨረሻም፡አንባቢው በቋንቋ በኩል ኢትዮጵያ ምን እንደምትመስል ይገነዘብ ዘንድ ባገሪቱ የሚገኙትን ቋንቋዎች ዝርዝር የሚያሳይ ጽሁፍ አቀርበናል፡፡

ስለአማርኛና ስለኦሮምኛ የቀረቡት ጽሁፎች አከ

ራካሪ ና ቸው::ከመጀመርያውም ሁለቱ ጸሁፎች አይስማሙም ምንም እንኳ ጸሁፎቹ የሚመለከቱት ዋና ነጥብ የቴክኒክ ጉዳይ ቢሆንም ዞርዞር ፖለቲካዊ ክርክርንና ውሳኔን ማስከተላቸው አንደማይቀር እናምናለን::ሰበተኛው ጸሁፍ በኢትዮጵያ የሚገኙት ቋንቋዎች ብዙ መሆናቸውን ያሳያል:: ባንዱ በኩል ይህ አስፈሪ ይመስላል::እንደውነቱ ከሆነ ግን የኢትዮጵያን የወደፊት ሬቮሉሽን ትልቅ ትርጉም ያለውና አስደናቂ ሊያደርጉት ከሚችሉት ነጥቦች ውስጥ አንዱ ይህ ነው:: 'የብሄሮች ቤተመዘከር' የሆነችውን ኢትዮጵያን ከፊውዳላዊ ወለል ከመውጣት የበለጠ የህይወት ምኞት ሌኖር እንደማይቻል ያስገነዝባል::

አንባቢዎቻችንን የምንለው ይህንን መጽሄት አንብበው እንደጨረሱ ላዘጋጁ በርቱ አስተያየታቸውን እንዲልኩ ነው::በዚህ ላይ በመመስረት የመጽሄት አዘጋጁ ብርዱ የወደፊት ስራውን በተሻለ መንገድ ለማካሄድ እድል ያገኛል::ሬቮሉሽን እንዲኖር ከተፈለገ ሬቮሉሽናዊ አስተሳሰብ በሰፊው ህዝብ ዘንድ እንዲሰራጭ ያስፈልጋል::ሬቮሉሽናዊ አስተሳሰብን ለማሰራጪት ደግሞ የህዝቡን ቋንቋ መናገር ያስፈልጋል::ቋንቋና ሬቮሉሽናዊ ትግል በጥብቅ የተሳሰሩ መሆናቸው ግልጽ ነው::



## የአማርኛ ቋንቋና ፊደል

ያማርኛ ቋንቋ መቼ መነገር እንደተጀመረ የሚያረጋግጥ ምንም ማስረጃ የለም::በአስራ አራተኛው መቶ አመት/ዓም/ የተጻፉ ነገሥታትን የሚያወድሱ አንዳንድ መዝሙሮች ተሰብስበው ታትመዋል::ይሁን እንጂ ከዚህ ጊዜ በፊት /ቢያንስ አምስት መቶ አመት/ አማርኛ ከትግሬ ደቡብ እስከሸዋ በሚገኘው በአማራ[1] ውስጥ ይነገር ነበር ብሎ ለመገመት ይቻላል::በአስራ ሰባተኛው መቶ አመት ግን ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሁሉ በይበልጥ ባገሩ ተስፋፍቶ የሚገኘው አማርኛ መሆኑ የታወቀ ነው::[2]

የአክሱም መንግሥት በስድስተኛው መቶ አመት መጨረሻ ግድም ከወደቀ በኋላ የነገሥታቱ መኖርያ በደቡብ ሆነ::አክሱም ከመውደቁ በፊት የአማርኛ ቋንቋ በደቡብ ሳይነገር አልቀረም ብሎ ለመገመት ይቻላል::ይህንንም ለማለት የሚያስደፍረው አማርኛ ከሌላ ግእዝ መሰል ቋንቋ እንጂ በእውነቱስ ከግእዝ የተወረሰ ስለማይመስል ነው::[3] ግእዝ ተናጋሪዎች እግእዝያን በአክሱም ላይ ሲስፋፉ ከበኋላቸው የመጡ ሌሎች የሴም ዘሮች ሌላውን ደጋውን ሰሜን ኢትዮጵያን በመያዝ አገውና ተናጋሪ ህዝብ ላይ ሠፈሩበት

አማርኛ ሴማዊ ቋንቋ መሆኑ አይካድም፣ነገር ግን ብዙ ኩሻዊ ቃላት፡ አባባሎችና ሰዋሰዋዊ ባህርዮች ተከሳልሰውበታል:: ከዚህም በላይ ከግእዝ ብዙ

ቃላት ወርሶአል::ከኩሽና የተገኘው ውርስ መጠን የቱን
ያህል መሆኑን የሚያረጋግጥ ጥናት ግን ገና አልተደረገም
ይልቁንም የተዋረሱት ቃላትና ሰዋሰዋዊ ባህርዮች የአማር
ኛ ቋንቋ አይነተኛ አካሎች ሊሆኑ ስለቻሉ ቀደም መሰረታ
ቸውን አጣርቶ ለማወቅ አይቻልም::

በአስራ ስድስተኛው መቶ አመትና ከዚያም በኋላ
በሚገኙት የኤውሮፓውያን የጽሁፍ ማስረጃዎች መሠረት አማ
ርኛ በሰፊው የሚነገር ቋንቋ መሆኑ ይታወቃል::ነገር ግን
ምንም እንኳ የቋንቋው መስፋፋት ባይካድም ለጽሁፍ አይ
ፈለግም ነበር::ነገስታቱ ቋንቋቸው አማርኛ ቢሆንም ዜ
ና መዋእላቸውን የሚያጽፉት በግእዝ ነበር::ከጥንት ጀም
ሮ ጸንቶ የቆየው ደንብ በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት
ተሽሮ የንጉሰ ነገስቱ ዜና መዋእል ለመጀመርያ ጊዜ በ
አማርኛ ተጻፈ::ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አማርኛ ለመጀመርያ ጊ
ዜ የጽሁፍ ቋንቋ ሆነ::በተለይም በምኒልክ ዘመነ መንግ
ስት አዋጆችና አንዳንድ መጽሀፍች በአማርኛ መውጣት ስለ
ጀመሩ ቋንቋው በይበልጥ መሰረት ያዘ::አስቀድሞ በኤርት
ራ ቀጥሎም በአዲስ አበባና በድሬደዋ ማተሚያ ቤቶች ከተ
ቋቋሙ በኋላ መጽሀፍትና መጽሄቶች ጋዜጦችም በብዛት መታ
ተም ጀመሩ::

## ፊደል

አማርኛ የሚጻፈው በግእዝ /ወይም የፈረንጅ ሊ
ቃውንት እንደሚሉት በኢቲዮፒክ/ ፊደል ነው::አማርኛ
በግእዝ ፊደል ከመቼ ጀምሮ መጻፍ እንደጀመረ ለማወቅ



አልተቻለም::

በጣም የታወቁትን የአለም ጽሁፎች በክርፊት በሶ
ስት ለመክፈል ይቻላል:: 1ኛ/ አልፋቤት 2ኛ/ ስአለ
ጽህፈት 3ኛ/ ፊደል::

አልፋቤት ሰው በንግግር አሳቡን ለመግለጥ ዥር
ሮውን: ሳንቃውን: አንደበቱን: ጥርሶቹን:ከንፈሮቹን
ወዘተ. በማቀናበር የሚገልጻቸውን ነጠላ ድምጦች የሚጸ
ፍበት ነው:: የኤውሮፓውያንና /ማለት የላቲን: የሲሪሊክ/
የአረብና ጽሁፎች አልፋቤት ናቸው::በነዚህ ጽሁፎች መ
ሠረት አንድ ድፍን ቀለም ለብቻዋ ስትመጣ አናባቢ ከሌ
ላት ምንም የተነባቢነት ሀይል የላትም:በስሟ ትጠራለች

በሥአል ጽሕፈት መሠረት አካል ያላቸው ነገሮች
ሁሉ ይሣላሉ::ረቂቅ ሀሳቦች ግን ድርጊትን በሚያመለክ
ቱ ያካል ንቅናቄዎች ወይም ምልክቶች ይታወቃሉ::የቻይ
ናና የጃፓን ጽሁፎች በዚህ ክፍል ውስጥ ይመደባሉ::

አንድ የፊደል ቀለም ሁለት ወይም ሶስት ያልፋ
ቤት ቀለሞችን ባንድነት አጠቃሎ ሊይዝ ይችላል::ለምሳ
ሌ—ካ—ka :ኳ kwa ወዘተ.

ፊደል ያላቸው ሌሎችም ቋንቋዎች አሉ::ነገርግን
በዚህ ላይ ስለግእዝ ጽሁፍ ብቻ እንናገራለን:: የግእዝ
ፊደል የሳባ ጽሁፍ ልጅ ነው:: ይህ ጽሁፍ ከክርስቶስ
ልደት በኋላ አራተኛው መቶ ዓመት ድረስ በአክሱም ጸን
ቶ ቆይቶ ነበር::ያክሱም ነገሥታት የተጠቀሙት በዚሁ
ጽሁፍ ነበር::

ክርስትና በአገሩ ከገባ በኋላ የሳባ ጽሁፍ ቀር ቶ በግእዝ ጽሁፍ መጻፍ ተጀመረ:: ጥንታዊ ግእዝ እን ደሳባ ጽሁፍ የማናበቢያ ምልክቶች ወይም አናባቢ ቀለሞች አልነበሩትም::ማናቸውም ቃል የሚጻፈው በድፍን ድምፅ ነበር::ይህን የመሰለው አጻጻፍ ሊያስከትል የሚችለው ችግር ግልጽ ስለነበር አንድ ቃል ሳይዛባ በትክክል የ ሚጻፍበትንና የሚነበብበትን ዘዴ መፈለግ ተጀመረ::በአ ክሱም [illegible] በይበልጥ ለምቶ ከኩሻዊ ቋንቋዎችም ተዳአ ኖ የተቀበለው ግእዝ ብዙ ልዩልዩ ድምጦች ስላፈራ የሳ ባን ጽሁፍ በጣም ማሻሻል አስፈላጊ ሆነ::

በ350 ዓ.ም ዘመ የግእዝ ጽሁፍ የማናበቢያ ምልክቶች ማድረግ ጀመረ: ወይም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ፊደል ሆነ::ይህ ከሆነ በኋላ ማናቸውም ቃል በትክክል ሊጻፍና ሊነበብ ስለቻለ እጅግ ጠቃሚ የሆነ እርምጃ ተደረገ:: 4/

የግእዝ ቋንቋ ከሞተ በኋላ አማርኛ በግእዝ ፊ ደል መጠቀም ጀመረ::ግእዝ በአማርኛ የማይገኙ ፊደሎች አሉት እነዚህም:- ሐ/ ጕሮር ነክ ሀ/: ኀ/ሳንቃነክ ሀ/: ዐ/ጕሮሮነክ አ/: ፀ/ የእንግሊዝኛ መሰል ድምፅ/::አማርኛም በግእዝ የማይገኙ ፊደሎች አሉት: እነዚህም:- ሸ ቸ ኘ ኸ ዠ ጀ ጨ ናቸው::

ይህን ጉድለት ለማሙዋላት አማርኛ እነዚህን ሰ ባት ፊደሎች ፈጠረ:: እነሱም በመሠረታቸው አዲስ አይ ደሉም::በግእዙ ፊደል ላይ የተመሰረቱ ናቸው::አመሰረ ታቸውም እንደሚከተለው ነው:- ሰ/ሸ: ተ/ ቸ: ነ/ኘ:ከ/ኸ: ዘ/ዠ:ደ/ጀ:ጠ/ጨ:: እነዚህ ፊደሎች በግእዙ ፊደል



ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ለማሳየት በፊደሉ ገበታ ላይ ቦታቸው ከየመሰራቶቻቸው ግርጌ ነው::

በአማርኛ ምንም ተግባር የሌላቸውን የግእዝ ፊ ደሎች ለማስወገድ በዚያን ጊዜ ምንም ሙከራ ያልተደረገ ይመስላል:: የሐ/ሀ/ኀ: የአ/ዐ ልዩነት የዚያን ጊዜ በግእዙም ጠፍቶ ነበር:: ነገር ግን ተግባር የሌላቸው ፊደሎች በግእዝ እንደታሪካዊ ቅርስ ተቆጥረው ተጠብቀው ስለቆዩ በአማርኛም ቢቆዩ ምንም አይደለም ተብሎ ይሆናል

የአማርኛ ፊደል በከፊል የአልፋቤትነት ባህርይ አለው::ይኸውም የያንዳንዱ ፊደል ሳድስ ነው::ሳድስ ያንዱ ቃል ጀማሪ ሲሆን ፊደል ነው::ነገር ግን ከቃል መጨረሻ ወይም የድምፅ ቅናት /አከሰንት/ ከሚነሳበት ፊደል ሲከተል ድፍን ድምፅ /ከንሰናንት/ ነው::ምሳሌ ትምህርት /təmhərt/: አትክልት /atkəlt/: ቤት / bét/

ይህ ህግ አንዳንድ ጊዜ የማይጠበቅበት አግባብ አለ::ይኸውም ግጥም ሲነበብ በመጨረሻው ሳድስ ላይ ብዙ ውን ጊዜ ቅናት እያደረጉ በማንበብ እንደፊደል ስለሚወ ሰድ ነው::እንዲሁም የጥያቄ ምልክት የሆነው 'ን' ሁል ጊዜ በቅናት ይነበባል::

የአማርኛ ድምጦች ሁሉ እያንዳንዳቸው ሰባት እና ባቢዎች አሉዋቸው: ማለት እያንዳንዱ ድምፅ ሰባት ተራ ና መልክ አለው::አማርኛ ሴማዊ ቋንቋ ቢሆንም በዚህ ረገድ ከሌሎች የሴም ቋንቋዎች ለምሳሌ ከአረብኛ ይለያል:

አረብኛ ሶስት አናባቢዎች ብቻ ነው ያለው::ያናባቢዎቹ
ብዛት የማይካድ ጥቅም አለው::የሆነው ሆኖ ምንም እን
ኳ አናባቢዎች ቢበዙም ርዝመታቸው እኩል ነው::ይህ ጉ
ድለት ሊሆን ይችላል::ነገር ግን ያናባቢ 'ርዝመትስጥረት'
ጉዳይ በአማርኛ እምብዛም ችግር ሊያስከትል አይችልም:
አልቻለም::

ችግሩ ሊነሳ የሚችለው በአማርኛ ፊደል ሌሎችን
ኩሻዊ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለምሳሌ ኦሮምኛን ለመጻፍ
የተሞከረ እንደሆነ ነው::እንደሚታወቀው በኦሮምኛ ያና
ባቢ ርዝምትስጥረት ትልቅ ሚና የሚጫወት ምእራፍ ነው::
አንድ አናባቢ በማጠር ፊንታ ከረዘመ ወይም በመርዘም
ፊንታ ካጠረ የቃሉን ትርጉም ይለውጠዋል::በአማርኛ ፊ
ደል የታተሙ ኦሮምኛ መጽሀፍ ቅዱስ ከሚታይበት ጉድለ
ቶች አንዱ ይህ ነው::

በተጨማሪ በአማርኛ ፊደል የሚታየው ግልጽ ጉድለት
የድፍን ድምፅ ማጥበቂያ ምልክት በሰፊው ያለመታወቅ ነው
ፊደሉን ለማሻሻል በተደረጉት ሙከራዎች ይህን ጉድለት
ለማሙዋላት ተሞክሮ ነበር: ነገር ግን ምንም ውጤት አል
ተከተለም::ነገር ግን ከሁሉም ይልቅ አቶ አዲስ አለማ
የሁ ያደረጉት ሙከራ መለስተኛ ውጤት እንደሚያስከትል
ተስፋ አለ:: 'ፍቅር እስከ መቃብር' በሚለው መጽሀፋቸው
ሊጠበቁ በሚገባቸው ፊደሎች ላይ አልፍአልፍ አንዳንዱ
ነጥብ አኑረዋል:: 5/

በአማርኛ ፊደል የሚታየው ሌላው ጉድለት የፊደሉ



ች ብዛት ነው::አማርኛ እያንዳንዳቸው ሰባት መልክ ያ
ላቸው 31 ፊደሎች አሉት: ድምራቸውም 217 ነው::
ከነዚህም ውስጥ ሊወገዱ የሚችሉና እንዲዉም በፍጹም አ
ገባብ የሌላቸው በድምሩ 44 ፊደሎች አሉ::እነዚህም
ከፊደሉ ጠቅላላ ድምር 20 በመቶ መሆናቸው ነው::የነ
ሱ መወገድ ቀጥሩን ሊቀንሰው ይችል ነበር::ዳሩ ግን
ምንም ሳንካ ህግ ባያስወግዳቸውም ልምድ በከፊል አስወ
ግዶአቸዋል::አንድ ጤነኛ ሰው /ሊዘንጥ ካልፈለገ በስተ
ቀር/ 'ሀያ' በማለት ፋንታ 'ሐያ:ኃያ:ኻያ' ብሎ አይ
ጽፍም::እንዲያውም 'ኻይለ ....' ብሎ የሚጽፍና ባዲስ
ዘመን ጋዜጣ የሚያሳትም ሰው ወጸለት 'ኃ'ግን አልሞተች
ም:ይገርማል!"እግዜር አወጣት" 'ኃይለ ....' ነው ያዳ
ናት::

ያማርኛን ፊደል ለማሻሻል ከተደረጉት ሙከራዎች
ሁሉ በመጨረሻ የተደረገው እጅግ የተሻለ ነው::ይህን
የማሻሻያ አሳብ ያቀረበው ኮሚቴ/ፊደል መሰረቱን ሳይለቅ
'ሰድስቶ' ያናባቢ ምልክቶች ህግ እንዲከተሉ ማድረግ ነበር
በኮሚቴው አሳብ መሰረት ይህ ህግ ከጸደቀ ፊደል ለመማር
የሚወስደው ጊዜ 89 በመቶ ይቀነሳል::ከዚህም በላይ
በአማርኛ የጽህፈት መኪና ላይ ያለው የቴክኒክ ችግር ይ
ቀላል ብሎ ያምናል::

የመማርያው ጊዜ እንደሚቀነስ የታወቀ ነው: የመ
ኪናውም የቴክኒክ ችግር ይወገዳል::ይህ ማሻሻያ በስራ
ከዋለ ጠቃሚነቱ የማይካድ ነው::ይሁን እንጂ ጥናቱ የማ
ጥበቂያ ምልክትን ጉዳይ በፍጹም አላሰበበትም::

አንዳንድ ሊቃውንት:ለምሳሌ ፕሮፌሰር አፈወርቅ: ኢኛሲዮ ጉዊዲ:ማርሰል ኮሄን:ውልፍ ሌስላው..ወዘተ. የሚጠበቁትን ፊደሎች ሁለት ነጥብ ይጭኑባቸዋል::ይህ ምልክት ለወደፊቱ እንደሚረጋ አይከዱም::በውጭ አገር ሊቃውንትና ሊንስቲቶቶች ዘንድ ይህ ምልክት ከጸና ብዙ ጊዜ ሆኖአል::

ያማርኛ ፊደል ሌሎችን ኩሻዊ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች:በተለይም ኦሮምኛን ሊያስጽፍ ይችላልን::በመሠረቱ ይህን ተግባር ለመፈጸም የሚያስችለው አቅም አለው::ኦሮምኛ ድፋትቀናት እንዲሁም ቀናት የሚበዙበት ቋንቋ ነው ይህ ድምፅ በአረፍተነገሮችም ሆነ በነጠላ ቃላት ላይ ይሰማል::

ያንዱ አረፍተነገርን ድፋትቀናት የማያውቅ:ከቃላት ላይ የሚነሣውን ቀናት እንዲሁም ያናባቢዎችን ርዝመትአጥረት የማያውቅ ባእድ አንባቢ ሊያነብ ቢሞክር አንዱ ኦሮሞ ተናጋሪ አዳማጭ በቀላሉ ሊገባው አይችልም::እንግዲህ ኦሮምኛ 1ኛ የድፋትቀናት ምልክት:2ኛ የቀናት ምልክት:3ኛ ያናባቢ ርዝመትአጥረት ምልክት ያስፈልገዋል ማለት ነው::ኦሮምኛ በላቲን አልፋቤት ቢጻፍም እነዚህ ፕሮብሌሞች ሙሉ መፍትሄ ሊያገኙ አይችሉም::የድፋትቀናት ምልክት ባማርኛም ሆነ በፈረንጅኛ የሚሠራበት አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው::

ከፍ ብሎ እንደተገለጠው ያናባቢ ርዝመትአጥረት ባማርኛ ፕሮብሌም አይደለም::በኦሮምኛ ግን አውራ ጉዳይ



ነው ለማለት ይቻላል::ኦሮምኛ በአማርኛ ፊደል ከተጻፈ ይህ ምልክት እንደአስፈላጊነቱ ሊገባ ይችላል::ማለት ለሚረዝሙት ፊደሎች የርዝመት ምልክት ሊደረግባቸው ይችላል::ይህን ለማድረግ አስቸጋሪ አይደለም::

1ኛ/ ከሚረዝመው ፊደል ራስጌ ወይም ግርጌ አንድ ምልክት ማድረግ: 2ኛ/ ከሚረዝመው ድምፅ ቀጥሎ አንድ ሌላ ፊደል /ከስራ ፊቶቹ ፊደሎች አንዱን: ለምሳሌ 'ጠ'ን/ማኖር::ሁለተኛው ዘዴ ከጸደቀ የሚረዝም ቃል ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ሊለይ ይችላል::

አጭር: ቡሌ ቢሌ ባሌ ቤሌ ቦሌ

ረጅም: ቡጡሌ ቢጢሌ ባጣሌ ቤጤሌ ቦጦሌ 7/

በኦሮምኛ 'ጠ'እና አጫፋሪዎቹ ከፊደልነት ተግባራቸው ተሽረው አናባቢ ማርዘሚያ ይሁኑ ስንል የሳይንቲፊክ ህግን መጣሳችንን አንክድም::ነገር ግን በፈረንጅኛም ቢሆን ሁለት ወይም ሶስት ቀለሞች በጣምራ አንድ ድምፅ እንዲሰጡ ሲደለደሉ የሳይንቲፊክ ህግን በመከተል አይደለም::በእንግሊዝኛ she የሚለው ቃል ሺ ተብሎ ይነበባል:: በሳይንቲፊክ ህክ ከሆነ ግን ሽሂ ተብሎ መነበብ ነበረበት::

ኦሮምኛ በላቲን ፊደል ከተጻፈ ሊያስከትለው የሚችል አንዳንድ ፕሮብሌሞች አሉ::በዚህ ቋንቋ የሚገኙ አንዳንድ ድምጦች ማለት: ቀ ጠ ጨ ጸ በላቲን አልፋቤት አይገኙም::እነዚህን ድምጦች በላቲን አልፋቤት ለመጻፍ

ሲፈለግ በዙ ምልክቶችን በማድረግ መይም ጥንድ ቀለሞችን አብሮ በማሰለፍ አንድ ድምፅ እንዲያገኙ ማድረግ ግድ ይሆናል::ይህ ያልፋቤቱን አባሎች ቁጥር ያበረክተዋል: ወይም ምልክቶችን ያበዛቸዋል:ይህም የህጻናቱን የመማሪያ ጊዜ ያስረዝመዋል::

የላቲን አልፋቤት ሀያ ስድስት አባሎች አሉት:: እነዚህም ሁለት መልክ አላቸው:— ትንሽና ትልቅ::ስንግዲህ ጠቅላላ ድምራቸው ሀምሳ ሁለት መሆኑ ነው::በቁም ጽህፈት የተጻፉ እንደሆነ ሀምሳ ሁለቱም ሀምሳ ሁለት ልዩልዩ መልክ አላቸው::እንግዲህ የላቲንን አልፋቤት የሚማር አንድ ህጻን ከመቶ በላይ የሆኑ ልዩልዩ መልኮች ማጥናት አለበት ማለት ነው:: የላቲን አልፋቤት የተማረ ህጻን <u>ማንበብ ባዲስ</u> መማር አለበት::

ከፍ ብለን እንደገለጥነው የአማርኛ ፊደል 217 አባሎች አሉት የሚባለው አነጋገር በሙሉ እውነት ሊሆን አይችልም::የሚከተሉት ፊደሎች:— ሸ.ኸ ዠ ጀ ጨ ቸ ኘ በሌሎች ላይ የተመሰረቱ ወይም የሌሎች ጥገኞች እንጂ ራሱን የቻለ መልክ የላቸውም::በፊደሉ ገበታ ላይ ነጻ ቦታ ሊሰጣቸው አይችልም::ከዚህም በላይ ሊወገዱ የሚችሉ ፊደሎች አሉ ብለናል:: ብቻ ይህንን እንተውና በአማርኛ ሀያ አራት መሰረታዊ ፊደሎች አሉ ብንል ስህተት አይሆንም::

የሀያ አራቱ መሰረታዊ ፊደሎች የመልክ አረባብ ከሞላ ጎደል ህግ የሚከተል ነው::ይህንም ለማየት ፊደሉን በስድስት ልዩልዩ መደብ መከፈል ይቻላል::1ኛ/ እ



ገር ያላቸው:/ ሸ ሰ ተ ወዘተ./ 2ኛ/ ቆሾች /ሀ መ ወዘተ./ 3ኛ አገዳሚዎች/ረ ፈ/:: በያንዳንዱ ክፍል ያሉት ዘይቤዎች ተመሳሳይ የርባታ ህግ ይከተላሉ:: የመጀመርያውና የሁለተኛው ክፍል 71–72 በመቶ ህጉን ይከተላሉ: በሶስተኛው ክፍል ያሉት ደግሞ 85–86 በመቶ ህጉን ይከተላሉ::ፊደሉ ታሪካዊ ተራውን ለቆ በርባታ ህግ ተከታይነት መሰረት ከተደለደለ እንዲሁም ስራፊት ፊደሎች ከተወገዱ የህጻናት የመማሪያ ጊዜ በጣም ሊያጥር ይችላል::

ፊደሉን ያጠና በቀጥታ ማንበብ ይችላል::እንደ ላቲን ፊደል 'ማገጣጠም' የሚባል ፕሮብሌም የለም::የቁም ጽህፈትና/የጁ ጽህፈት/ የማህተም ጽህፈት የተለያዩ አይደለም::ስለዚህ ከላቲን ፊደልና ከአማርኛ ፊደል ለህጻናት ወይም ለተማሪ የሚከብደው የትኛው ነው ቢባል ያለ ጥርጥር የላቲኑ ነው::

ወደምልክቶቹ እንመለስ::ምልክት የሚያስፈልገው ፊደል የሚጠብቅበትን: ድፋተቁናትን ያናባቢ ርዝመትን ለማሳየት ነው::ይህን ሁሉ ፍላጎት የሚያጠግብ ጽሁፍ የለም::ጽሁፎች ሁሉ ጎደሎዎች ናቸው::እርግጥ ነው ቋንቋው ሳይዛባ: አንድ ነቁጥ እንኳ ሳትገድል እንዲጻፍ ሲፈለግ ይህን ለማድረግ የሚያስችሉ 'አለምአቀፍ የፎኔቲክ አልፋቤት' የሚባል አለ::ነገር ግን ይህ አልፋቤት ላንዳንድ ሳይንሳዊ ጽሁፍ እንጂ ለዘወትር አገልግሎት አያገለግልም::

አንድ ሰው የናት ቋንቋውን በልምድ ደህና አድ
ርጎ ያውቃል::ዱፋተቀናቱን: ያናባቢ ርዝመትአጥረቱን:
ቀናቱን የቃላት አገባቡን ከህጻንነቱ ጀምሮ ስለሚያውቅ
ለዚህ ሰው ይህ ችግር አይሆንበትም::ምልክት ማድረግ
አይጠቀመውም::ለምሳሌ ያረበናን ቋንቋ እንውሰድ::አረ
ብኛ ሰበት መሠረታዊ አናባቢዎችና የማጥበቂያ ማሳያ አ
ለው::እነዚህ በጽሁፉ ራስጌና ግርጌ የሚውሉ ጭረቶች
ናቸው::አንድ ጽሁፍ ያሳንዳቸ ውዝግብ በትክክል እንዲ
ነበብ በተፈለገ ጊዜ ምልክቶቹ ሁሉ ይሠፍራሉ::ቁርዓን
በነዚህ ምልክቶች በሙሉ ይጠቀማል::የመማሪያ መጽሀፍች
ም እነዚህ ምልክቶች አሉባቸው::ነገርግን የነዚህ ምል
ክቶች ሁልጊዜ ሠፍሮ መገኘት አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ
ያለምልክት ይጻፋል::በጋዜጦችና በሌሎች ተራ ጽሁፎች
ምልክቶች አይደረጉም:ቋንቋውን የሚያውቁት ሰዎች ምልክ
ት አያስፈልጋቸውምና::

እንግዲህ ወደሌሎች ኩሻዊ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች
ና በተለይም ወደኦሮምኛ እንመለስ::የኦሮምኛ መጽሀፍቅዱ
ስ የተጻፈው ባማርኛ ፊደል ነው::ከዚህ መጽሀፍ አንድ
ምእራፍ መርጦ ኦሮምኛ የማያውቅ ሰው ሲያነበው አንድ
ኦሮሞ እንደያዳምጥ ቢደረግ ኦሮሞው በሙሉ ሊገባው አይ
ችልም::ነገርግን እርሱ ራሱ ቢያነበው ሊገባው ይችላል:
ምክንያቱን ገልጠናል::

ኦሮምኛ ባማርኛ ፊደል ቢጻፍ ፊደሉን የሚያውቅ
ነገርግን ኦሮምኛ ቋንቋቸው ያልሆነ ሰዎች በቀላሉ ሊያ
ነቡት ይችላሉ ማለት አይቻልም::እንዲሁም ኦሮምኛ በላ



ቲን አልፋቤት ቢጻፍ ላቲን አልፋቤትን የሚያውቁ ሁሉ
በቀላሉ ሊያነቡት አይችሉም::እንግዲህ ለቋንቋው ባእድ
የሆኑ ሰዎች ቋንቋውን ለመማር ሲፈልጉ ምልክቶች ያስፈ
ልጓቸዋል::ከተማሩት በኋላ ግን ያለምልክቶች ሊያነቡት
ይችላሉ::

ያማርኛን ፊደልና የላቲንን አልፋቤት ጉደሎነት
እንዘነጋም::ገና ያልተጻፈ አንድ የኢትዮጵያ ቋንቋ ከ
ሁለቱ አንዱን መርጦ ቢወስድ እነዚህን ጉድለቶች ማሟላ
ት አለበት::ነገርግን ጉድለቱ በላቲን አልፋቤት እን
ደሚበልጥ ለማሳየት ሞክረናል::

ገና ያልተጻፉ ብዙ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አሉ:
እነዚህን ቋንቋዎች ባማርኛ ፊደል ለመጻፍ ከመሞከር በ
ፊት የያንዳንዱን ቋንቋ ባሕርይ አስቀድሞ ማጥናት ያስ
ፈልጋል::ምልክት ያስፈለገው እንደሆነ የሚያስፈልገውን
አስገብቶ ባማርኛ ለመጻፍ ይቻል እንደሆነ መሞከር ነው።
ነገርግን ይህን ከማድረግ በፊት ካማርኛና ከላቲንኛ ጽ
ሁፍ የተኛው ለተማሪዎች እንደሚቀና አስቀድሞ ሳይንሳዊ
ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋል::

1. አማራ ማለት የጂኦግራፊ እንጂ የዘር መታወቂያ አልነበረም::ከጐጃምና ሸዋ በስተቀር አማርኛ የሚነገርባቸው ሰሜናዊ ያገሩ ክፍሎች በደፈናው አማራ ይባሉ ነበር::አሁን ግን በዚህ ስም የሚጠራው በወሎ ጠቅላይ ግዛት የሚገኝ አማራሣይንት የሚባለው ቦታ ብቻ ነው::

2/ Pero Pais: História da Etiópia Vol.I. p. 18 (Livraria Civilizacão Editora, Porto, 1945

3/ Marcel Cohen: Traité de la Langue Amharique, p.13 (Paris, 1936)

4/ Hans Jensen: Die Schrift in Vergangenheit und Gegenwart,(DVW) Berlin 1958, p. 326.

5. <u>ፍቅር እስከ መቃብር</u> ገጽ 9::/አቶ ሐዲስ የፊደል መጥበቅ ጠቅላላ አግባብ ያልገባቸው ይመስላሉ፤ ፊደሉ የሚጠብቀው ገቢርና ተገብሮን ለማሳየት ብቻ አይደለም::አንዳንዱ ግሶች በባሕሪያቸው ጠባቂ ናቸው::/

6/ Journal of Ethiopian Studies ,Vol. VIII, No.1, Jan.1970( Addis Ababa)

7/ እነዚህ ለምሳሌ እንዲያመቹን የተጠቀምንባቸው ልብወለድ ቃላት ናቸው::



## የኦሮሞን ቋንቋ እንዴት እንጻፈው::

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶችን ባማርኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች—በተለይም ለመጀመር ያህል በትግራይና በኦሮሞ ቋንቋዎች—ለማውጣት ካቀደ ዛሬ ሶስት ዓመታት አለፉዋል:: ስለዚህ ነገር የመጀመሪያው ውሳኔ የተደረገው በ1968(1) በዛግሬብ ጉባዔ ላይ እንደነበር ይታወሳል::ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መጽሄቶችን በትግራይና በኦሮሞ ቋንቋዎች ለማውጣት እየታሰበ እስካሁን ነገሩ ሳይሳካ ቀርቷል::ይህ የሆነበት አንደኛው ምክንያት የቴክኒክ ጉድለት ነበር:: ማለት:ያማርኛ ጽሁፎቻችንን ወደሌሎቹ ቋንቋዎች ሊተረጉሙ የሚችሉ:ወይንም ጽሁፎችን በነዚያ ቋንቋዎች ሊደርሱ የሚችሉ ሰዎች አልተገኙም፤ቢገኙም ደግሞ ቋንቋዎቹን በጽሕፈት መኪና ለመሥራት አልተቻለም ነበር::በተለይ የትግራይን ቋንቋ በሚመለከተው በኩል አንዱ ዋና ችግር ይህ ሲሆን:ኦሮምኛን በሚመለከተው በኩል ግን ሌላም ችግር ነበር::ይህውም የፊደል ችግር ነው::ኦሮምኛን በግእዝ /አማርኛ/ ፊደል እንጻፍ ወይ ለሚለው ጥያቄ መልስ ሊሰጥ አልተቻለም::በነዚህ ምክንያቶች ከማህበራችን እስከዛሬ አንዳችም መጽሄት በትግራይም ሆነ በኦሮሞ ቋንቋዎች ተጽፎ አልወጣም::

አሁን ባለንበት ጊዜ መጽሄቶቻችንንም ሆኑ ሌሎችን ጽሁፎች በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጽፎ ማሠራጨት በጣም አስፈላጊና አስቸኳይ ነገር ሆኗአል::

አንደኛ ነገር በኢትዮጵያ የሚደረገው የብሄሮች ትግል ዛሬ ከፍ ወዳለ ደረጃ ደርሶአል:: የኤርትራ: የባሌ: የአፋርና የሌሎችም ክፍለ አገሮች ህዝቦች የመሣርያ ትግላቸውን አስፋፍተዋል::ይህንን ትግል በፖሊቲካ ይዞ ከፍ ለማድረግ ከተፈለገ ከህዝቡ ከራሱ ውስጥ የሚወጡት መሪዎች የተማሩና ሌሎችን ለማስተማር የሚችሉ መሆን አለባቸው::እነደርሱ ለመሆንና ለማድረግ ደግሞ ሬቮሉሽናዊ ቲዎሪን በገዛ ቋንቋቸው ለማጥናት እድል እንዲኖራቸው ያስፈልጋል::ስለዚህ ጽሁፎችን በየቋንቋው ማሰራጨት ዛሬ አስፈላጊና አስቸኳይ ሆኖአል::

ሁለተኛ ነገር በሰፊው ህዝብ ደረጃ: የጥንቱን የድንቁርናና የጭለማ አለም ለመደምሰስ የሚያስችለው ካሁኑ ጽህፈትንና ንባብን ማስተማር በመጀመር ነው::ፊውዳሊዊው ስርአትና የቀደሙትም ሌሎች አድሀሪ ስርአቶች ህዝቡን ጨቁነው: ረግጠው ለመበዝበዝ የቻሉት ድንቁርናን እንዳለ በመጠበቅ መሆኑን እናውቃለን::ያሁኑን የህዝባችንን የጨለማ አለም ደምስሰን በቦታው የነቃ: የራሱን እድል በእጁ የጨበጠ: ራሱን የቻለ አለም ለመተካት ከፈለግን ሬቮሉሽናዊ አሳቦችን ካሁኑ በሰፊው ህዝብ ዘንድ ማሰራጨት አለብን::ይህ ድንቁርናን ጨርሶ የመደምሰስ ግብ የረጅም ጊዜ ግብ ሲሆን: አሁን ባለንበት ጊዜ ደግሞ ሰፊው ህዝብ የትግሉን አላማ ተረድቶት እንዲሰለፍ ለማድረግ ሬቮሉሽናዊ አሳብን ማሰራጨት ግዴታ ነው

በዚህም በኩል ነገሩ አስፈላጊና አስቸኳይ መሆኑ ግልጽ



ይመስለናል::

በዚህ ሁኔታ ማህበሮቻችን አሁን በደረሱበት ደረጃ በሚገባ ተጣጥረው የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ማቅረብ ግዴታቸው ነው::ከፊታችን ያሉትን ችግሮችና መሰናክሎች በተቻለ ፍጥነት አሸንፈን ወደፊት መራመድ አለብን በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የኦሮሞን ቋንቋ ችግሮች ስናቀርብ ነገሩ በብዙዎች ዘንድ አሳብንና አስተያየትን በመቀስቀስ ተፈላጊውን ውጤት ያስገኛል በማለት ተስፋ አድርገን ነው::በጠቅላላው የቋንቋዎቻችን አጻጻፍ የሚመለከት ጽሁፍ በመጽሄቶቻችን ሲወጣ የመጀመርያው ጊዜ ነው:: በተጨማሪም የዚህ ጽሁፍ ደራሲ የቋንቋን ሳይንስ አጥርቶ የሚያውቅ ሰው አይደለም::ከነዚህ ምክንያቶች የተነሣ ከዚህ በታች የቀረቡት አሳቦች ብዙ ጉድለትንና ስህተትን እንደሚይዙ አይጠረጠርም::ነገር ግን ጽሁፉ ስለዚህ ጉዳይ አሳብ በገባቸው ሰዎች ሁሉ ዘንድ የመሰራት ፍላጎትን ካስገኘ ከግቡ ደርሶአል ለማለት ይቻላል::

## 1. በኦሮምኛ እስከዛሬ የተጻፈ ስለ

በኦሮምኛ ቋንቋ ወይንም ስለኦሮሞዎች ለመጀመርያ ጊዜ የተጻፈው እኤአ በ1840 ገደማ ይመስላል::ክራፕፍ የተባለው ሚሲዮናዊ በ1842 በእንግሊዝ አገር የኦሮሞ ቋንቋ መዝገበ ቃላት: በእንግሊዝኛና በኦሮሞ አሳትሞአል::እንደዚሁም ቱቴከ የተባለው ጀርመናዊ በባርነት ተሸጠው በኋላ እንዳጋጣሚ ወደጀርመን ከተወሰዱ ስስት ኦሮሞዎች ቋንቋውን ካጠና በኋላ አንድ መዝገበቃላትን

እንዲሁም አንድ የሰዋሰው መጽሀፍን ለማሳተም ሲዘጋጅ በመ
ካከሉ ስለሞተ: ወንድሙ /የቶቸክ ወንድም/ ጸሁፉን ሰ
ብስቦ በ1844 የኦሮምኛ: የእንግሊዝኛና የጀርመንኛ
መዝገበ ቃላት አሳትሞአል::የቶቸክ መጽሀፍ ከወጣ በኋላ
ባውሮፓ አንዳንድ ሚሲዮናውያንና መንገደኞች እንደዚሁ
ስለኦሮሞ ቋንቋ ጽፈዋል::እዚህ ላይ ግን ሁሉን ሳይሆን
ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ እንፈልጋለን::

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የታወቀው ቄስ አባ ማ
ስያስ በ1867 አንድ ትልቅ ያማርኛና የኦሮምኛ ሰዋሰው
በላቲን ቋንቋ ጽፎ አሳትሞአል::ይሁን እንጂ በኦሮምኛ
ተጽፈው ከሚገኙት ጽሁፎች ሁሉ ሰፊና ትልቅ የሆነው የኦነ
ሲሞስ ነሲብ 'መጻፈ ቁል ቁሉ' /መጽሀፍ ቅዱስ ነው::/2/

ቶቸክን ኦሮምኛ ያስተማረች ኦሮሞዎች በባርነት
የተሸጡ እንደነበሩ ሁሉ: ከተጠመቀ በኋላ ኦኔሲሞስ የተ
ባለውም የወለጋ ኦሮሞ በባርነት የተሸጠ ሰው ነበር::
ስምንት ጊዜ ከተሸጠ በኋላ በ1870 ምጽዋ ሲደርስ የታ
ወቀው የቀኝ ገዢዎች ቀኝ እጅ የነበረውና በኋላም በአ
ጻል የተገደለው ሙንትሲንገር የተባለው ሰውዬ ኦነሲሞስን
/ገዝቶ ሳይሆን አይቀርም/ በሞንኩሉ: በምጽዋ አጠገብ:
ለሚገኙ የስዊድን ሚሲዮናውያን ወስደ ሰጠ::እነዚህ ሚ
ሲዮናውያን ካስተማሩትና ካጠመቁት በኋላ ወዳገራቸው ሰ
ደውት ከ1876 እስከ 1881 አስተማሩት::/3/

ሙሉ መጽሀፍ ቅዱስን ከመተርጐሙ በፊት ኦነሲሞስ
አንዳንድ መጽሀፍትን በኦሮምኛ ቋንቋ አሳትሞአል::ለምሳሌ



የወንጌል: ጸሎትና መዝሙር መጽሀፍ በ1887 በሞንኩሉ:
አዲስ ኪዳንንም እዚያው በ1893: እንደዚሁም በጣም
ጠቃሚና በትምህርት የተሞላውን የኦሮምኛ ንባብ መማርያ
በ1894:: የኦሮምኛው መጽሀፍ ቅዱስ የታተመው በስዊስ
አገር በባዝል አጠገብ በ1899 ነው::......ኦነሲሞስ
የሞተው በ1931 ሲሆን ዋና ረዳቱና የኦሮምኛ አዋቂ
የነበረችው አስቴር የሞተችው አሁን በቅርቡ በ1962
ነው::/4/

የኦሮምኛ መጽሀፍ ቅዱስ እስከ ቅርብ ዘመን ድ
ረስ በወለጋ ወንጌላውያን/ፕሮቴስታንቶች/ ዘንድ በሰፊው
ይሰራበት ነበር::ከዚያ ወዲህ ግን መንግስቱ እንዳይሰ
ራበት ስለከለከለ አሁን በኢትዮጵያና በተለይም በወለጋ
መጽሀፉ የሚገኘው አልፎ አልፎ ነው::...... የመጀመ
ርያው የኦሮምኛ መጽሀፍ ከታተመ ከመቶ ሰላሳ አመቶች
አልፈዋል::በኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ የነበረውና ዛሬም
ያለው ስርአት ፊውዳላዊ የጨለማ ስርአት ከመሆኑ የተነ
ሳ እንኳንስ ኦሮምኛ የተጻፈ ቋንቋ ሆኖ ሊዳብር: የጥ
ንት ሀበሻም ቋንቋዎች አማርኛና ትግራይ በሚገባ ሳይዳ
ብሩ እስከዛሬ ደርሰዋል::

የኦነሲሞስ የመጽሀፍ ቅዱስ ትርጉም ከታተመ
በኋላበዚህ በሀያኛው ክፍለ ዘመን አንዳንድ የኦሮምኛ
መጽሀፍት ታይተዋል::ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ጠቅሰን
ይዘታቸውን ባጭሩ በንመለከት ጠቃሚ ይመስላል::

በ1913 ፋት የተባለው እንግሊዛዊ በጣም ጠቃሚ
የሆነ የእንግሊዝኛና የኦሮምኛ መዝገበ ቃላት አሳተመ::
ሆድሰንና ዎከር የተባሉ ሁለት እንግሊዛውያን በ1922
ያሳተሙት የኦሮምኛ ሰዋሰው /5/መጀመርያውኑ የተሰራው
ለእንግሊዝ ነጋዴዎች ነበር:: 'በሀበሻ አገር ለሚነገ
ዱ ሰው ጋሎኛን ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነውና'/6/መጽሀፉ
የተጻፈው በላቲን ፊደል ሲሆን አልፎ አልፎ አማርኛም ይ
ገኝበታል::በተለይ በመጨረሻው የኦሮሞ ግሶች በእንግሊ
ዝኛና በአማርኛ ተተርጉመው ተዘርዝረዋል:: የአ[illegible]ኛው
ግስ የተጻፈው በአማርኛ ፊደል ነው::በጽሁፉ የታገመባ
ቸው ፊደሎች አገባብ ግን የእንግሊዞች የተሰራ እንጂ
በድምጽ ጥበብ/ፎነቲክስ/ ላይ የተመሰረተ አይደለም::
በሰዋስውም በኩል የቀረበው ፈጽሞ አያጠግብም::ይሁን
እንጂ ቋንቋውን ለመማር ለፈለጉ እንግሊዛውያን ጠቃሚነት
ሳይኖረው አልቀረም: ብዙ የንግግር ልምዶች አሉበትና::

በዚሁ አመት /1922/ኤንሪኮ ቼሩሊ የተባለው
የታወቁ የኢትዮጵያ አጥኚ ኢጣሊያዊ ሊቅ 'የደቡብ አ
በሻ ጋሎች ህዝባዊ ስነጽሁፍ' የሚል መጽሀፍ አሳተመ::
/7/ይህ መጽሀፍ የታሪክ ግጥሞችንና ዘፈኖችን: የዘመ
ቻ: የፍቅር: የሰርግ: የህጻን አሹሩሩ የበአሉና የሃ
ይማኖት መዝሙሮችን ወዘተ. ይዘአል::በተጨማሪም ስለ19
ኛው ነጻ የኦሮሞ መንግስታት: ስለገዳ ስርአት አሰራርና
ስለኦሮሞ ልማዶች አንዳንድ ጽሁፎች ይገኙበታል::

ቼሩሊ የግጥሞቹንና የታሪኮቹን ትርጉም በእንግ



ሊዝና ሰጥቶአል::ይሁን እንጂ: ምንም እንኳ ሰውዬው
በታወቀ የድምጽ ምልክቶች ለመጠቀም ቢሞክርም: አጻጻፉ
አንዳንድ ቦታ ላይ ፈጽሞ አይነበብም::ግጥሞቹን ከነገ
ረት ሰዎች ሲያዳምጥ በሚገባ ያልሰማቸው ድምጾች ስላሉ
ይህ ብዙ ስህተቶችን አስከትሎበታል:: የዚህ መጽሀፍ ዋ
ና ጥቅሙ የኦሮሞን ባህልና ታሪክ በመጠኑም ቢሆን ማስ
ፈሩ ነው::

ቀጥሎ ሊጠቀስ የሚገባው መጽሀፍ ሞሬኖ የተባለው
በኢጣሊያን ቅኝ አገዛዝ ውስጥ ትልቅ ሹመት የነበረው
ሰውዬ በ1939 ያሳተመው የሰዋስው መጽሀፍ ነው::ሞሬ
ኖ ቀደም ብሎ በ1935 የሸዋኦሮሞዎችን ዘፈን የያዘ
'የጋላ ተረትና ግጥም' የሚል መጽሀፍ አሳትሞ ነበር::
/8/ይህ ሰውዬ በኢትዮጵያ በሙሉ ብዙ ከመዞሩ የተነሳ
ሌሎቹንም ኩሻዊ ቋንቋዎች አጥንቶአል:: የኦሮሞንም ልዩልዩ
ክፍሎች ያጠና ይመስላል::በተጨማሪም የቋንቋ ትምህርት
/ሊንጉዊስቲክስ/ ያውቅ ነበር::ይህ ሁሉ እውቀቱ በመጽ
ሀፉ ውስጥ ይታያል::ይሁን እንጂ መጽሀፉ ለኢጣሊያ ቅ
ኝ አገዛዝ ይመች ዘንድ በጥድፊያ ስለተሰራ ብዙ ስህተ
ቶችና ጉድለቶች አሉበት:: የተሰራው ሰዋስው የተሙዋላ አ
ልነበረም::በተለይ ደግሞ የዚህን ጽሁፍ አላማ —ያጻጸ
ፍን ነገር— በሚመለከተው በኩል: ምንም እንኳ ጽሀፈቱ
ከነቀከር የሚሻል ቢሆንም: አሁንም አጥጋቢ ሆኖ አልተገ
ኘም::

ዳ ቲዩኔ የተባለው የካቶሊክ ቄስ በ1939 በ

ሀረር ከተማ የኦሮምኛና የኢጣሊያንኛ መዝገበ ቃላት አሳተሞአል::/9/ይህም መጽሀፍ፡ ሰንደምሬና መጽሀፍ ሁሉ፡ የተሰራው የኢጣሊያንን ቀኝ አገዛዝ በቶሉ አንዲያጠነክረው ታስቦ ነበር::በጽሀፉ በመጀመርያው ላይ አጭር የኦሮምኛ ሰዋሰው ይሰጣል::በመጨረሻም አንዲሁ የኢጣሊያንኛና የኦሮምኛ ቃላት ደርድሮአል::መጽሀፉ በግምት ከሰምንተሺ አስከ አስርሺ የሚሆኑ የኦሮምኛ ቃላትን ይዘአል::ይሁን አንጂ የተጻፈው በኢጣሊያንኛ ድምጽ በመሆኑ ይህንን ቋንቋ ለማያውቁ ሰዎች በመጽሀፉ መጠቀም ያስቸግራል::

አንዱ የመጨረሻ መጽሀፍ::ይህውም ኖርድፌልት የተባለ የስዊድን ሚሲዮናዊ በ1947 በስዊድን ያሳተመው የኦሮሞ ሰዋሰው ነው::/10/ይህ መጽሀፍ ከላይ ከተጠቀሱት ሁሉ የሚለይበት አንድ ነገር አለ::ሰዋሰዉ የተገለጸው በእንግሊዘኛ ሲሆን ኦሮምኛው ግን የተጻፈው ባዓርና/'የጋሻ ፊደል' ይለዋል ደራሲው/ፊደል ነው::ይህ ብቻ አይደለም::ኖርድፌልት የሰዋሰዉን አገላለጽ የመሰረተው በዚሁ ፊደል ላይ ነው::ማለት እንደቦታውና እንደሁኔታው አንዱ የንግግር ክፍል /ስም ተውላጠ ስም ወዘተ./ ሲለወጥ የትኛው ፊደል ከግእዝ ወደራብእ ወይንም ከሳልስ ወደሳልስ እንደሚለወጥ ይናገራል::

ኖርድፌልት እንደቀደሙት ደራሲዎች ሁሉ ብዙ ስህተቶችን ቢያደርግም መጽሀፉ ከሁሉም ስለሚሰፋ ጠቃሚነት አለው::ይሁን እንጂ እዚህ የሚመለከተንና ወደፊትም የምናየውን ያጻጻፍ ችግር ከማመቃለት የራቀ ነው::



ከረጅሙ ባጭሩ በኦሮምኛ ወይም ስለኦሮምኛ የተጻፉትን ዋና ዋና መጽሀፎች ከዚህ በላይ ጠቀስን::በጣም ጥቂቶች ናቸው::የሁንና ወደፊት አዲስና ለሰፊው ህዝብ የሚያገለግለ ያጻጻፍ ዘዴ እንዲፈጠር ከተፈለገ ከዚህ በላይ የጠቀስናቸውን መጽሀፎችና ሌሎችንም ስለዚሁ ጉዳይ የተደረሱ ጽሁፎችን አበጥሮ አጥንቶ ይዘታቸውን በግልጽ የሚያመለክት የቋንቋ አጥኚ ቡድን መፈጠር ይኖርበት ይሆናል::ለወደፊቱ ብዙ ስራ አለ::

## 2. የኦሮምኛ ድምጾች ባህርይ

አንዱን ቋንቋ እንዴት እንጻፈው ማለት በቋንቋ ውስጥ ባሉት ድምጾች ምን አይነት የሚታይ ድምጽ እንስጣቸው ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው::በመሰረቱ ጽሁፍ /ፊደል/ የንግግር፡ የድምጽ ምልክት ነው::ባንዱ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙት ድምጾች በቁጥር በጣም የተወሰኑ ናቸው:: ብዙውን ጊዜ እንደቋንቋው አይነት ከሰላሳ እስከ ሃምሳ ይሆናሉ::ቃላትና አረፍተነገር የሚገነቡት እነዚህን ጥቂት ድምጾች በልዩልዩ ሁኔታዎችና አሰራሮች በማገጣጠም ነው::እንግዲህ የፊደል ነገር ለነዚህ ተደጋጋሚ ለሆኑት ድምጾች ምልክት መስጠት ብቻ ነው::በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በቀጥታ የሚመለከተን ጉዳይ ይህ ስለሆነ የኦሮምኛን ሌሎች ባህርዮች ወደጐን ትተን የድምጾችን ባህርይ ብቻ እንመለከታለን::ከዚያ በፊት ግን ስለኦሮምኛ ቋንቋ ቦታ ትንሽ እንጥቀስ::

የኢትዮጵያንና የሌሎችን ያፍሪካ አገሮች ቋንቋ

ዎች ያጠኑ የውጭ አገር ሰዎች ለምናን ኩሻዊ/11/—
ኩሺቲክ—ቋንቋ ይሉታል::የቋንቋ ቀዴዎች የቋንቋዎችን
ድምጾች:ዜማዎቻቸውን/ቶንስ/:ዱፋና ቀናት/ስትሬስ/:
የቃላት አመሠራረት:የሰዋስው አቀነባበር—ማለት:የነጠላና
የብዙ መለያ:የተባእታይና የአንስታይ ጾታ መለያ:የስም
ን አለዋወጥ/ሙያ ወይንም 'ኬዝ'/:የተውላጠስምን አሠ
ራር:የግሥን አርባታ...ወዘተ.—ያጠኑ ቋንቋዎቹን ይ
ለዩአቸዋል::የሚዛመዱትን ባንድነት አድርገው ስም ይሰ
ጧቸዋል::በዚህ መሠረት ኦሮምኛ ኩሻዊ ቋንቋ ነው ሲባ
ል ከቤጃ:ከአገው:ከቢሌን:..ይዛመዳል ማለት ነው::
እነዚህ ሁሉ በባሕርያቸው የሚመሳሰሉ ኩሻዊ ቋንቋዎች
ናቸው::እንደዚሁም አማርኛ:ትግርኛ:ትግሬ:ጉራግኛ:አደ
ርኛ..ወዘተ. ሴማዊ ቋንቋዎች ይባላሉ::

በንደር የተባለው አሜሪካዊ በኢትዮጵያ ያሉትን
ኩሻዊ ቋንቋዎች እንደሚከተለው ይዘረዝራል::/12/

የሰሜን ኩሻዊ—ቤጃ
መካከለኛ/ወይንም የአገው/ ኩሻዊ—አውንጊ:ቅማ
ንት:ቢሌን:ዛማታንጋ
የምሥራቅ ደጋ ኩሻዊ/—ሀዲያ:ሊቢደ:ከምባታ:አ
ላባ:ሲዳሞ:ደራሳ:ቡርጂ:
የሰሜን ቆላ ኩሻዊ—አፋር ሳሆ
ኦሮሞ ሰሜን—ቦረና:ቆቱ:መጫ
ሌሎች ቆንሳዊ—ቆንሶ:ጊደሌ:ቡሳ
ደቡብ—ማጉጉደ:ኢራቀው:አርቦሬ:ደሰነች
ሌሎች ወሪዛያዊ—ጋዋዳ:ጉበዜ:ወርዜ:ፂማይ
ሶማሳዊ—ሶማሌ:ባይሶ:ሬንዲሌ:ቦኒ



ማለት በኢትዮጵያ ከ25 በላይ የሆኑ ኩሻዊ
ቋንቋዎች አሉ::እንደዚሁም 15 ያህል ሴማዊ ቋንቋዎች

ከአርእስታችን ውጭ ቢሆንም እዚህ ላይ ከበንደ
ር ጥናት አንድ ነገር እንጥቀስ::በንደርና ጓደኞቹ መ
ሠረታዊ ቃላት/ቤዚክ ቮካቡሌሪ/ ብለው 98 ቃሎች ከ
መረጡ በኋላ የነዚህን ቃላት ትርጉም በኢትዮጵያ ቋንቋ
ዎች ሁሉ ሰበሰቡ::ከዚህ በኋላ እነዚህን ቃላት በማመ
ሳሰል:የትኛው ቋንቋ ከየትኛው ጋር የበለጠ ወይም ያነ
ሰ እንደሚዛመዱ አሳይተዋል::በዚህ መንገድ:ለምሳሌ:ካ
ማርኛና ከትግርኛ ቃላት 56 በመቶው:ከትግርኛና ከትግ
ሬ 64 በመቶው:ከሶማሌና ከቆቱ/ኦሮሞ/ 27 በመቶው:
...ወዘተ. እንደሚመሳሰሉ አገኙ::የኦሮምኛን ክፍሎች
በሚመለከተው በኩል የመጫና የቆቱ 81 በመቶ:የመጫና
የቦረና 79 በመቶ:የቦረናና የቆቱ 88 በመቶ መመሳሰ
ላቸውን አሳዩ::ይህንን የጠቀስንበት ምክንያት እንደት
ግሬና ትግርኛ:እንደልዩልዩዎቹ የኦሮምኛ ክፍሎች ያሉት
ቋንቋዎች:እንደዚሁም ከረጅም ዘመናት በኋላ እንደአማር
ኛና እንደትግርኛ ያሉት ቋንቋዎች ሊዋሀዱ እንደሚችሉ
ለማስታወስ ያህል ነው::...

ወደኦሮምኛ ድምጾች ባሕርይ እንመለስ::ድምጾች
ን በሚመለከተው በኩል ኦሮምኛ በጠቅላላው አምስት እና
ባቢዎች/ዋየሎች/ አሉት::ኢ:ኤ:አ:ኦ:ኡ::/አማርኛ
ሰባት አሉት—በተጨማሪ የግእዝና የሳድስ አናባቢዎች/
እንደዚሁም:ከሌሎች ቋንቋዎች በውሰት የተወሰዱትን ካል
ጨመርን:ኦሮምኛ 23 ያህል ድፍንድምጾች/ኮንሶናንትስ/

አሉት::እነ [illegible]:ፐ:ሸ:ዠ በመሠረቱ በቋንቋው ውስጥ የሉም::በተጨማሪ:ኦሮምኛ ባማርኛ ቋንቋ ውስጥ የማይገኝ የምላስን ጫፍ ወደላንቃ አዙሮ በማስነካትና ወደውስጥ በመተንፈስ የሚሠራ አንድ ድፍንድምጽ አለው::በኦነሲሞስ መጽሀፍና በኋላም በኖርድፊልት ሲጻፍ ደ ተብሎ ነው እንግዲህ በቋንቋውስጥ የሚገኙት ዋና ተደጋጋሚ ድምጾች 28 ያህል ናቸው ማለት ነው::

በመጀመሪያ ያናባቢዎቹን ባሕርይ እንመልከት:: በኦሮምኛ ያናባቢዎች ርዝመትና አጥረት የቃላት /ማለትም የነገሮች/ መለያ ስለሆነ በጣም ትልቅ ቦታ አለው:: አንዳንድ ምሳሌዎች እንውሰድ::/ከፊደሎች አናት ላይ የሚደረገው ሠረዝ የማራዘሚያ ምልክት ነው::/

ላ̄ፋ/lāfa /—ለስላሳ እና ላፋ/lafa /—መሬት
አ̄ዱ/ādu/—ማቃሰት እና አዱ/adu /—ፀሀይ
ኤ̄ጋ/ēga/—መጠበቅ እና ኤጋ/ega /—ከንግዲህ
ዲሱ/disu/—መወጠር እና ዲ̄ሱ/dīsu/—መተው
ኦ̄ኡ/ōu /—መራራት እና ኦኡ/ou /—መሞቅ
ቁ̄ፋ/qūfa/—ጥጋበኛ እና ቁፋ/qufa /—ባል

የሚለዩት ባናባቢ ርዝመት ነው::ቋንቋው በነዚህ ዓይነት ነገሮች የተሞላ ስለሆነ ምሳሌ በብዙ ለመስጠት ይቻላል::ዳላ/dāla, dala, dalla/:ጋራ/gāra, gara, garā / ...እነዚህ ሁሉ ቃላት ልዩልዩ ነገሮች ናቸው::ያናባቢው ዓይነት ያው ሆኖ የሚሰጠው ርዝመት ወይም አጥረት ብቻ ልዩ ትርጉም ያስከትላል::

ያናባቢዎች መጠን/ርዝመት—አጥረት/ የነገሮች



መለያ ብቻ ሳይሆን በኦሮምኛ ሰዋስዉም ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ ይዞ ይገኛል::አንዳንድ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል:ከኦሮሞ መስተዋድዶች ብዙዎቹ የሚለዩት በዚሁ ነው:: ኬሳ/kēssa/ 'ውስጥ': ኬሳ/kēssā/ 'ከውስጥ': ኢራ /irra / 'ላይ': ኢራ/irrā / 'ከላይ': ቢራ/bira / 'አጠገብ': ቢራ/birā / 'ከአጠገብ'....ናቸው::

ይህ ብቻ አይደለም::አንዳንድ የቃላት ተቀጥላዎች /ፓር ቲከሎች/ እንደተቀጠሉበት ቃል አባባል ርዝመታቸውን ይለውጣሉ::ለምሳሌ —ኦታ የሚለው ተቀጥላ የብዙ ቁጥር መስርያ ነው:: —ዎች እንደሚለው ያማርኛ ተቀጥላ:: —ኦታ /ōta/ ብዙውን ጊዜ ረጅም ኦ አለው: ግን እርሱ የሚከተለው አናባቢ ረጅም ከሆነ እርሱ ራሱ ያጥራል:: ሀዳ /hāda/እናት: ሀዶታ/hādota/እናቶች:: ነገር ግን ሀቱ/hattu /ሌባ:ሀቶታ/hattōta/ሌቦች:: ማና /mana/ ቤት: ማኖታ/manōta/ቤቶች::ነገር ግን: ሞቲ /mōti / ንጉስ: ሞቶታ/mōtota/ንጉሶች:

እንደዚሁም በግስ እርባታ ውስጥ ያናባቢዎች ርዝመት የጊዜ መለያ ነው::አዴሚ/ ሄደ/ ሀላፊ ጊዜ ነው አዴሚ/ ሂድ/ቦዝ አንቀጽ ነው::

በኦሮምኛ ቋንቋ ረጅም አናባቢዎች ብዙውን ጊዜ የድምጽ ከፍታም/ስትሬስ/አላቸው::ይሁን እንጂ የድምጽ ከፍታና ዝቅታ ባጭር አናባቢዎችም ላይ ይገኛል:: በሌላ በኩል ደግሞ የድምጽን መዳከምና መቆጥ የሚያስከትሉ የቃላት አግባቦች አሉ::በዚህ መንገድ የኦሮሞን አናባቢዎች በስበት ለመመደብ ይቻላል::የሚዳከሙ/ የሚቆጡ/

አጥር ሆነው ድምጽ ከፍታ የሚያሳዩ: ረጅም ሆነው የዱ
ምጽ ከፍታ ያሳያቸው::

| የሚዋጡ | አጥርና ክፍት ዱ. | ረጅምና ክፍት ዱ. |
| --- | --- | --- |
| | | ኢልካን/ilkân/ጥርስ |
| ማና /man$^a$/ቤት | ዋጋ/waggá/አመት | አደሙ/adêmu/መሄዱ |
| አደሜ/adêm$^e$/ ሂደ | ሀሬ/harré/አህያ | ፊጤ/fîṭe/ጧፍ |
| አደሚ/adêm$^i$/ ሂዱ | ጅርቢ/jirbí ጥጥ | ጉቱ/gûtu/ሙሉ |
| | ሊልሞ/lilmó/መርፌ | ሆዱ/hôdu/እንካ |
| | ጋልቱ/galtú/ደደብ | |

በእውነቱ ብዙ ምሳሌዎች ለመስጠት ይቻላል::እዚ
ህ ላይ በሚገባ ለማስረዳት የምንፈልገው ያናባቢዎች ር
ዝመትና እጥረት የቋንቋው መሠረታዊ ባህርይ መሆኑን ነው
በዚህም ባህርዩ ኦሮምኛ ካማርኛና ከሌሎችም ሴማዊ ቋንቋ
ዎች አጅግ የተለየ ነው::

አናባቢዎች የቋንቋ ዋና ድምጾች በመሆናቸው አ
ነርሱን በመጠኑ ተመለከትን እንጂ የድፍን ድምጾችንም
ርዝመትና እጥረት በቋንቋው ውስጥ እንደዚሁ የቃላት ወ
ይንም የነገሮችና የሰዋሰው ክፍሎች መለያ ነው::/እዚ
ህ ላይ 'ርዝመትና እጥረት' ስንል ባማርኛ 'መጥበቅና
መላላት'ከሚለው ጋር አንድ መሆኑን እናስታውስ::በቋንቋ
ባይገስ ድፍን ድምጾች ይረዝማሉ ወይም ያጥራሉ ሲባል
መጠናቸው ''ቻ ተለውጦ አይነታቸው ግን ያው ነው ማለት
ነው::/ ማዳ/mada/ ቁስል: ማዳ/madda/ የወንዝ ውሀ:
ሉቡ/lubu/ነጻ ማውጣት: ሉቡ/lubbu/ነፍስ: ጃላ/jāla/
ወዳጅ: ጃላ/jalla/ጠማማ:ራኮ/rako/በጋብቻ የሚደረግ መሥ
ዋእት:ራኮ/rakko/ችግር:ባዳ/bada/ብዙ:ባዳ/badda/ደጋ:..
.. የሚለዩት በድፍንድምጾቹ መጠን ነው::በሰዋሰውም ው
ስጥ ሀቴ/hate/ሠረቀሁ:ሠረቀ:ሀቴ/hatte/ሠረቀህ:ሠረ
ቀች: እና እነዚህን የመሳሰሉ ሁሉ የሚለዩት እንደዚሁ
ነው::የድፍንድምጾችን መጠን በሚመለከተው በኩል ኦሮም
ኛና አማርኛ በጣም ይመሳሰላሉ::አንድ ምሳሌ ለመስጠት
ያህል:ባማርኛ ሰዋሰው ብዙዎቹ አድራጊና ተደራጊ ግሶች
የሚለዩት በዚህ ነው::መበተን:መበተን:መመሥረት:መመሥ
ረት:መጻፍ:መጻፍ...ወዘተ.::ቃላትን ወይንም ነገሮች
ን በመለየት በኩል የድፍንድምጾች ሚና/ሮል/ ካማርኛ
ይልቅ በኦሮምኛ በርግጥ ይበዛል::

እንግዲህ የኦሮምኛ ድምጾች ባሕርይ ከዚህ በላ
ይ ባጭሩ ተጠቀሰ::ለማጠቃለል:በዚህ ቋንቋ ውስጥ የድ
ምጾቹ—አናባቢም ሆኑ ድፍንድምጾ—መጠን ወይንም ርዝመት
ና እጥረት መሠረታዊ ነገሮች ናቸው::የቋንቋው ድርና
ማግ ናቸው ለማለት ይቻላል::ጥያቄው ይህንን መሠረታዊ
ባሕርይ በሚገባ የሚገልጹ ምልክቶችን የመፍጠር ጉዳይ ነው

## 3.ኦሮምኛ ባማርኛ ፊደላት

ያማርኛ ፊደሎች ለራሱ ላማርኛ ቋንቋ ብዙ ችግ
ሮችን እንደያዙ የታወቀ ነገር ነው::ከዚህም የተነሣ
ብዙ የማሻሻያ ዘዴዎችና እቅዶች ከዚህ በፊት ቀርበው
ማንኛቸውም እስከዛሬ ከሥራ ላይ አልዋለም::እዚህ ላይ

በሊፈደሉቹ ችግሮች ሳንዘረዝር አንባቢው እራሱ በዚሁ መጽሄት ውስጥ በሌላ ቦታ የሰፈረውን እንዲያነብ እንጋብዘዋለን::እዚህ ላይ ለማየት የምንፈልገው ያማርኛ ፊደሎች ለኦሮምኛ ውለው ምን ውጤት እንደሰጡ ነው::

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው በኦሮምኛ ከታዩት መጻሕፍት ውስጥ ዋናው ባማርኛ ፊደል የተሠራው የኦነሲሞበ መጽሀፍቅዱስ ነው::የኦነሲሞስን አጻጻፍ የመረጠው ኖርድፈልት ያጻጻፉን ጉድለቶች ሲገልጽ የሚከተሉትን ነጥቦች ያነሣል::

"የተለያዩ ቃላትን የማሳጠርና የማጋጠም ዝንባሌው/የኦነሲሞስ/ ግንው የትርጉሞቹ ሁሉ ችግር ነው:: ከዚህም የተነሣ ጋሎቹ እራሳቸው የራሳቸውን ቋንቋ ማንበብ ያዳግታቸዋል:ለባእዳማ እነዚህ አህጽሮቶችና መገጣጠሞች ብዙውን ጊዜ የተለቀ ጣጣ ምንጭ ናቸው::"/13/ ይልና ለዚህም አንዳንድ ምሳሌዎችን ይሰጣል::

"ማሉን ሰጉዴ = ማል አን ሰጉዴ"
"ሰሩኩቶንፈዱ = ሰሩኩቶ እንፈዱ"
"እሳንትመን = እሳንት ሀመን፤
"ኝሞንንአርጉ = ኝሞን አንአርጉ"

በስተግራ የተጻፉት የኦነሲሞስ:በስተቀኝ ያሉት የኖርድፈልት "ሰርማቶች" ናቸው::በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የኦነሲሞስም የኖርድፍልትም አጻጻፎች አጥጋቢ አይደሉም:: ደግሞም ኖርድፈልት ላረፍተነገሮቹ የሰጠውን.ትርጉም ስንመለከት እራሱ የሰዋሰው ስሕተት እንዳደረገ ለማየት ይቻላል::ይሁን እንጂ ቃላትን ባህጽሮት የማቀረብ ወይ



ንም ሁለትሶስቱን ገጣጥሞ የመጻፍ ነገር ትልቅ ችግር አይፈጥርም::እላይ በተሰጠው በድምጾች ባሕርይ ውስጥ ይህንን ጉዳይ ያላነሣነው በዚህ ምክንያት ነው::ነገሩን ኖርድፈልት ካነሣው:እዚህ ላይ በኦነሲሞስ እንደማይፈረድበት ለመጥቀስ እንወዳለን::ኦሮምኛ ሲነገር አንዳንድ ቃላት በርግጥ ከሌሎች ቃላት ጋር አንድነት ተያይዘው ይሰማሉ::ከዚህም የተነሣ አንዳንድ የግድ ከሌሎች ጋር መጻፍ የሚኖርባቸው ቃላት አሉ::ለምሳሌ ያህል:የኦሮሞ ተውላጠስሞች አንዳንድ ጊዜ ከሚከተላቸው ግሥ ጋር ተገጥመው ቢጻፉ ንግግርን በበለጠ ያሳያሉ::እላይ ኖርድፈልት ከጠቀሳቸው ምሳሌዎች ውስጥ "ሲሩኩቶ" የሚለው ባንድነት መጻፉ ጥሩ ነገር ነው::....የሆነሆኖ: እላይ እንደተባለው ይህ ጉዳይ ትልቅ ችግር አይደለም::

ኖርድፈልት በኦነሲሞስ ላይ ካቀረባቸው ሂሶች ዋና መስሎ የሚታየን "ኦነሲሞስ በሣልሥና በሣድስ ወይንም በግእዝና በራብእ መካከል ልዩነት አያደርግም፡የሚለው ነው::ኦነሲሞስ በሣድስና በግእዝ የተጠቀመው አጭር "ኢ"ንና አጭር "እ"ን ለማመልከት ነው::ሣድስ/በድፍንድምጽነቱ ሳይሆን ባናባቢነቱ/ እና ግእዝ በኦሮምኛ ቋንቋ ውስጥ እንደሌሉ እላይ ገልጸናል::በሌላ በኩል ደግሞ ያማርኛ ፊደላት አጭርና ረጅም አናባቢዎችን የሚያሳዩበት ምልክት እንደሌላቸው የታወቀ ነው::ከዚህም የቲነሣ ኦነሲሞስ ባንድ ቦታ በሣልስ የጻፈውን በሌላ ቦታ በሣድስ:በግእዝ የጻፈውን በራብእ ከመጻፍ ሊያመልጥ አልቻለም::የኦሮሞን ረጅምና አጭር አናባቢዎች

ባማርኛ ፊደላት ለመግለጽ ስነሥሞስ የነበረው ምርጫ በ
ጣም አስቸጋሪ እንደነበረ ለመረዳት የሚቻለው በዚህ ነ
ው::አይፈረደበትም::/በነገራችን ላይ ሰዎች አማር
ኛን ቢናገሯ 'ንፍጥ' በማለት ፈንታ 'ኒፍጥ'::'ከረመ
በማለት ፈንታ 'ካራማ'... የሚሉት በዚህ ምክንያት ነ
ው::/ በተረፈም ሂሉን ያቀረበው ናርዶፈለት ራሱ 'አ
ናባቢዎች ረዥምና አጭር ለመሆን ይችላሉ' ብሎ ከማለፍ
በስተቀር ለዚህ ችግር በመጽሀፉ ውስጥ አንዳችም መፍት
ሄ አልፈጠረለትም::ስለዚህ አርሱም ያው እንደስነሥሞስ
ነው ለማለት ይቻላል::

በጠቅላላው ስንመለከተው የስነሥሞስ አጻጻፍ ፊ
ጽሙ አጥጋቢ አልነበረም::ይህንን ለማስረዳት መጽሀፍቅ
ዱስን ከማንኛውም ገጽ ላይ ከፍቶ ለመመልከት ይቻላል::
ያለውን መዓት ችግር በበለጠ ለመረዳት ከተፈለገ እንዲ
ያውም ያማርኛን ፊደል ለማንበብ የሚችል ሰው ፈልጎ
መጽሀፍቅዱሱን ለማንበብ እንዲሞክር ማድረግ ነው::ናር
ዶፈለት 'ጋሎቹ ራሳቸው የራሳቸውን ቋንቋ ማንበብ ያዳ
ግታቸዋል' ብሎ የጻፈው እስከምን ድረስ እውነት እንደ
ሆነ ለመረዳት የሚቻለው ያን ጊዜ ነው::አንዳንዱ ም
ሳሌዎችን በመጥቀስ ችግሮችን እናመልከት::መኃልየመኃል
ይ:የሰሎሞን የፍቅር መዝሙር:የምእራፍ ፫ መጀመሪያ እ
ንደሚከተለው ተጽፍአል::

'ሀልከን አፈተከረት ሎጉንክ እስስጃለቴ በርባዔ
በርባዔ ደቤስ::ናንከዓ መንደራጃፍ ገባ ኬስ
ወሉዓ ኬሰስ ሎጉንክ እስስጃለቴ ነንበርባዓ::
በርባዔ:ደቤስ::



ባማርኛው መጽሀፍቅዱስ የዚህ ትርጉም እንደዚህ
ነው:— 'ሌሊት በምንጣፌ ላይ ነፍሴ የወደደችውን ፈለ
ግሁት::ፈለግሁት አላገኘሁትም::እነሣለሁ በከ
ተማይቱም እዞራለሁ:ነፍሴ የወደደችውን በጉዳና
ና በአደባባይ እፈልጋለሁ::ፈለግሁት:አላገኘሁ
ትም::'

ለመጀመር ያህል በግልጽ የሚታየውን አንዱ ጉድለት እን
መልከት::'የወደደችው' የሚለው በሰርምኛው 'እስስጃለ
ቴ' ተብሎ ነው የተጻፈው::ነገርግን ይህ አጻጻፍ የጾ
ታን መዘበራረቅ ያስከትላል::'ለ' በጥብቀት ከተነበበ
በርግጥ 'የወደደችው' ያሰኛል:ሳልቶ ከተነበበ ግን
'የወደደው' ማለት ነው::እንደዚሁም 'በርባዔ' የሚለ
ው ወይ አንደኛና ሶስተኛ ሰው ተባእታይ:ወይንም ሁለተ
ኛና ሶስተኛ ሰው አንስታይ ሊሆን ይችላል::ማለት 'ፈ
ለግሁ:ፈለገ' ወይንም 'ፈለግህ:ፈለገች'::እነዚህን
በሰርምኛው የሚለያቸው የ'ዔ' መጥበቅና መላላት ብቻ
ነው::በተጨማሪ ከጾታው ሌላ:ሰውም እንዲለይ ከተፈለገ
—ማለት በ'ፈለግሁ' እና በ'ፈለገ' መካከል ልዩነት
እንዲደረግ ከተፈለገ—በዚህ አረፍተነገር ውስጥ የግድ
ተውላጠስም መግባት ይኖርበታል::ያለበለዚያ ግን ፈላጊ
ው ማን እንደሆነ ለመረዳት አይቻልም::'በርባዔ ደቤስ'
የሚለው አረፍተነገር 'ፈለግሁ አጣሁም' ወይንም 'ፈለ
ገ አጣም' ተብሎ በሁለት ሊተረጐም ይችላል::/ባማርኛ
ቋንቋ ውስጥ በዚህ ምሳሌ ለጾታ መዘባረቅ ፈጽሞ ቦታ
የለም::በሌላ ቦታ ግን ይህው ችግር አለ::ለምሳሌ:

እንደምትሄዱ፡እንደምትበሳ...እንተ፡እንቿ ካለተጨመረበ
ት ገለጸ አይሆንም፡፡/

ባጭር 'አ' ፊንታ በግእዝ የተጻፈው የሚያስከ
ትለውን ትልቅ የንባብ ችግር ወደጐን ብንተወውና ባማር
ና ፊደሳት የተጻፈው ስንዴት መነበብ እንዳለበት ብንመ
ለከት፡በነዚህ ጥቂት አረፍተነገሮች ውስጥ ስንት የንባ
ብ ችግር እንዳለ ለማየት እንችሳለን፡፡'አሬ ተከረተ'
በሚለው ውስጥ 'ረ' እና 'ተ' መጥበቅ አለባቸው፡፡
'ሎጉንከ' በሚለው ውስጥ 'ጉ' መጥበቅና መርዘም አለ
በት፡፡'ኳለቴ' በሚለው ውስጥ ለ እና ቴ መጥበቅ አለ
ባቸው፡፡...'ጋሎቹ አራሳቸው የራሳቸውን ቋንቋ ማንበ
ብ' እንዲያዳግታቸው ያደረገው የእነሲሞስ አጻጻፍ የያ
ዟቸውን ችግሮች ባጭሩ ተመለከትን፡፡ነገርግን፡እሳይ እ
ንደተባለው ሁሉ፡ ጥፋቱ የእነሲሞስ ባይሆን ያማርኛ ፊ
ደሎች ለኦሮምኛ ለመዋል ባለመቻላቸው ነው፡፡ የዛሬ ሰባ
ዓመት የተጻፈውን የእነሲሞስን መጽሀፍ ትተን የኖርዱፊ
ለትንም መጽሀፍ ብንመለከት ችግሮቹ ያው ናቸው፡፡እንዲ
ያውም አሁን በቀርቡ ከተጻፈ ጽሁፍ ምሳሌ በመውሰድ የ
ችግሮቹኝባሕርይ የማይለውጥ መሆኑን ለማሳየት እንችሳለ
ን፡፡

በጃንዋሪ 1969 በወጣው 'የኢትዮጵያ ጥናትና
ምርመራ መጽሄት'/ቮልዩም 7፡ ቁጥር1/ ውስጥ አንዱ
አብዱራህማን ሞሀመድ ኩራም የሚባል ደራሲ ሁለት መቶ
የቆቶ ኦሮሞ ምሳሌዎችን ባማርኛ ፊደሎች ጽፎ አውጥቶአ
ል፡፡እንግሊዝኛ የሚያውቅ ሰው ከምሳሌዎቹ ሥር የተሰጡ



ትን ትርጉሞች እያነበበ ኦሮምኛውን ይረዳ ይሆናል፡፡እ
ንግሊዝኛን የማያውቅ፡ያማርኛን ንባብ ብቻ የሚችል ኦሮ
ሞ ግን ምሳሌው የትኛው እንደሆነ ለመረዳት እያንዳንዱ
ን ቃል ሶስትአራት ጊዜ ደጋግሞ ማንበብ ይኖርበታል፡፡
ያለበለዚያ ነገሩ ሊገባው አይችልም፡፡

እነዚህን የኦሮሞ ምሳሌዎች አንዱ ባንዱ ብንመ
ለከት ደስ ባለን ነበር፡፡ግን እዚህ ላይ እንደርሱ ማ
ዱረግ የሚያስፈልግ አይመስለንም፡፡ጥቂት ምሳሌዎች፡ከሁ
ሉ ጉልተው የሚታዩትን ጉደለቶች ለማስተዋል ብቻ፡እንጥ
ቀስ፡፡በ83ኛውና በ84ኛው ምሳሌዎች ውስጥ ሁለት 'ሶዳ'
ተብለው የተጻፉ ቃላት እናገኛለን፡፡ደራሲው እንደሚያመለ
ከተው የመጀመሪያው 'ፊሪ' ማለት ነው፡ሁለተኛው ግን
'አማቸ' ማለት ነው፡፡ግን የሁለቱም አጻጻፍ ያው ነው

ነገርግን ከዚህኛውም የበለጠ ለማለት የምንፈል
ገውን የሚያሳይ ምሳሌ 95ኛው ነው፡፡እንደሚከተለው ተ
ጽፎአል፡—

ተከ ቶፉን ኒርመ፡ለመ ቶፉን ሀርመ፡፡

ከዚህ በፊት እንዳደረገነው ሁሉ ባጭር 'ኦ'
ፊንታ ግእዝ ፊደል በመጻፉ የሚያስከትለውን የማይካዱ
የንባብ ችግር ወደጐን ብንተወውና የማጥበቅ—ማሳሳቱን
ችግር ብቻ ብንመለከት፡ይህ ተረት ሁለት ልዩ ትርጉሞች
ን ሊሰጥ ይችሳል፡፡ደራሲው የሰጠው ትርጉም 'ኢንዴ መ
ፍሳት /ሰውነት?/ ወንድነት ነው፡ሁለቴ መፍሳት እህያ
ነት ነው' የሚለውን ሲሆን፡ ተረቱን ሰምቶ የማያውቅ ሰ
ው ግን 'አንዴ መምጣት ወንድነት ነው፡ሁለቴ መምጣት

አህያነት ነው·ብሉ ሊረዳው ይችላል::በመፍባትና በመም
ጣት መካከል የሚለየው ያናባቢ ርዝመት ብቻ ነው::....

ከዚህ በላይ በተሰነዘሩት ነገሮች ሁሉ ለማስረ
ዳት የፈለግነው ያማርኛ ፊደል አሁን ባለበት ሁኔታ ፈ
ጽሞ ለአሮምኛ ቋንቋ ሊውል የማይችል መሆኑን ነው::አ
ንዱ ድምጽ ከሌላው እንዴት እንደሚለይ በጽሁፍ ለማስረ
ዳት መሞከር ቀላል ነገር አይደለም::በተለይም ኢንተር
ናሲዮናሳዊ የሆኑትን ፊደሎች ከነድምጻቸው አንባቢ የማ
ያውቃቸው ከሆነ::ይሁን እንጂ:ቢያንስ ቢያንስ ያማርኛ
ን ፊደሎች ማንበብ የሚችሉ አሮሞዎች ሁሉ ከላይ ያሰፈ
ርነውን ቢያነቡ የምናቀርበው ጥያቄ እንዴት ከፍተኛ እ
ንደሆነ ሲረዱታ ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

ያማርኛ ፊደላት አሁን እንዳሉ ለአሮምኛ /ምና
ልባትም ለሶማሊኛና ለሌሎች ኩሽ ቋንቋዎች/ ፈጽሞ ሊ
ውሉ አይችሉም::ይህንን ከተረዳን እንግዲህ አሮምኛን
የመጻፊያ ዘዴ የግድ ማግኘት አለብን::በዚህ ደራሲ አ
ስተያየት:በዚህ በኩል ከሶስት መንገዶች አንዱን ለመም
ረጥ ይቻላል:—1ኛ/ያማርኛን ፊደሎች አሻሽሎ ለአሮምኛ
ም ሆነ ለሌሎች ቋንቋዎች የሚያገለግሉ ማድረግ::2ኛ/
በላቲን ፊደላት ላይ የተመሠረተውን ኢንተርናሲዮናሳዊ
ፊደል መውሰድና ለቋንቋው ማዋል::3ኛ/አራሱን የቻለ
አዲስ ፊደል መፍጠር::

### 4. የምርጫ ጉዳይ::

የተማሪ ማህበር—ለዚያውም በውጭ አገር የምንገ
ኝ—ከመሆናችን የተነሣ ከሰፊው ሕዝብ ጋር እንዳችም ግ



ንኙነት የለንም::በሕዝቡ መካከል ብንሆን ኖሮ ከላይ
የተጠቀሱትን ሶስት ዘዴዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ ከሥራ ላ
ይ በማዋል የትኛው መንገድ ተስማሚ እንደሆነ በሳይንሳ
ዊ ምርመራ ለማረጋገጥ በቻልን ነበር::ሥራው ቀላል ነው
ንባብንና ጽህፈትን ለመማር እድሜያቸው የሚፈቅድላቸውን
ሕጻናት በብዛት ወስደ ከሶስት ቦታ ከከፈሉ በኋላ በያ
ንዳንዱ ቦታ አንዱን ዘዴ ብቻ ማስተማር ነው::በዚህ
መንገድ የትኛው ፊደል ባጭር ጊዜ ውስጥ እንደተጠና:የ
ትኛው ለሕጻናቱ በበለጠ ለንባብና ለጽሕፈት እንደተመቸ:
...ወዘተ. ለማረጋገጥ በተቻለ ነበር::ነገርግን ለጊ
ዜው የዚህ ዓይነቱን ሳይንሳዊ ምርመራ ለማከናወን እድ
ል የለንም::ባገርቤት በዩኒቨርሲቲ የሚገኙት ጓደኞቻችን
ወይንም ለዚህ ነገር የሚቀረቀሩና ሥራውን ለማከናወን
ፈቃደኝነትና ችሎታ ያላቸው ሰዎች በቀርቡ ሠርተውት ው
ጤታቸውን እንደሚያስታውቁ ብዙ ተስፋ እናደርጋለን::

አሁን ባለንበት ሁኔታ ከሶስቱ መንገዶች የትኛ
ው ይሻላል ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው መልስ መቶ በመቶ
ሳይንሳዊና የተሟላ ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው::ይ
ሁን እንጂ የሚታየንን ማቀረቡ ትክክለኛውን ዘዴ የምና
ገኝበትን ቀን ያፋጥነዋል እንጂ የሚያስከትለው ጉዳት
ስለሌለ ከዚህ በታች አስተያየት ለመስጠት ተገፋፍተናል::

1ኛ/ያማርኛ ፊደላት ሳማርኛ ቋንቋ ለራሱ የያ
ዙት ችግሮች በዚሁ መጽሂት ውስጥ በሌላ ቦታ ተገልጸዋ
ል::እነዚህን ችግሮች እዚህ ላይ እንደገና አናነሣም::
ይሁንና ያማርኛ ፊደላት ተሻሽለው ለአሮምኛ ሊውሉ ይች

ሳሉ ከተባለ የመሻሻያው ዘዴ የሚከተሉትን ነጥቦች የሚ
ያረካ መሆን አለበት::/ሀ/ ያናባቢው የ'እ' አጭር መ
ልክ መፈጠር አለበት::ማለት ያማርኛው ግእዝ ፊደል ሁ
ሉ—መ:ሠ:ረ:ሸ:ቀ...ወዘተ.—እንዳች ምልክት ወስደ
ያጭር 'እ'ን ድምጽ ማሰማት ይኖርበታል::ያለበለዚያም
ፊደሎቹ እንዳሉ ሆነው:እነሱ ነሷሙስ:እነኖር ዱፊልት እን
ደተቀመጡባቸው ሁሉ:ለኦሮምኛው አጭር 'እ' መቆም አለባቸ
ው::ይህ ሊያስኬድ ይችላል:ነገርግን ኦሮሞዎች ያማርኛ
ን ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ:ፊደሎቹ እነዚያው ስለሆኑ:አ
ማርኛን አጣምመው በኦሮምኛ ድምጽ እንዲናገሩት ይገደዳ
ሉ::/ከላይ የተጠቀሰውን የኦሮሞዎችን አማርኛ ማስታወስ/

/ለ/ የቀሩትን አናባቢዎች የሚያረዝሙና የሚያሳ
ጥሩ ምልክቶች መፈጠር አለባቸው::ማለት ኦሮምኛ ባማር
ኛ ፊደሎች ከተጻፈ በያንዳንዱ ፊደል ላይ እነዚህ ምል
ክቶች መቆም ይኖርባቸዋል::ለምሳሌ ያህል ሠረዝን/—/
እንደማርዘሚያ:ክብን እንደማሳጠሪያ ብንወሰድ 'እሰሰኛ
ለቲ' የሚለውን ቃል 'እሰሰኛ̄ለቲ̊' ብለን መጻፍ ይኖር
ብናል::ያው እንግዲህ በ/ሀ/ የተጠቀሰው መሻሻያ ከ
ገባበት በኋላ ነው::የዚህ ዓይነቱ አጻጻፍ የሚያስከት
ለውን የጊዜና የጉልበት መባከን መረዳት አያዳግትም::

/ጠ/ የድፍንድምጾችን መጥበቅ የሚያሳይ ምልክ
ት መፈጠር አለበት::አቶ ሀዲስ ዓለማየሁ ያቀረቡት አ
ንድ ነጥብ ከፊደሉ አናት ላይ እንዲደረግ:ወይንም ሌሎ
ች ያቀረቡትን የሁለት ነጥብ ለመውሰድ ይቻሉ ይሆናል:
ለምሳሌ 'ይቻል' የሚለው 'ይቻ̇ል' ወይንም 'ይቻ̈ል'



/መ/ የድምጽን ድፋትና ቀናት የሚያሳዩ ምልክቶ
ችም መፈጠር ይኖርባቸው ይሆናል::...

ባጭሩ:ሌሎቹን ያማርኛ ፊደሎችን ችግሮች/የፊደ
ሎቹን መብዛት:የያንዳንዱ ፊደል ያገሣሥ ልዩነት.../
እንኳን ወደጎን ትተን መሻሻያ ሲሆኑ የሚችሉትን ከዚህ
በላይ የጠቀስናቸውን ዘዴዎች ከሥራ ላይ ለማዋል ብንፈ
ልግ ጣጣው ይጨምራል እንጂ በምንም በኩል ጥቅም እንደ
ማያስገኝ ግልጽ የሆነ ይመስለናል::ኦሮምኛንም ሆነ ሌ
ሎችን ኩሻዊ ቋንቋዎች ባማርኛ ፊደላት መጻፍ ጥቅም ሊ
ኖረው ይችላል ቢባል:የወደፊቷ ሕዝባዊት ኢትዮጵያ ሕዝ
ቦች አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ መማር ከኖረባቸው ፊ
ደሉን እንደገና መማር አለማስፈለጉ ብቻ ነው::ነገርግን
ይህ ጥቅም ከጉዳቶቹ ወይንም እንደጭነት ከሚከብዱት ች
ግሮቹ ጋር ሲመዛዘን ዋጋ ያጣል::ስለዚህም ኦሮምኛን
ባማርኛ ፊደሎች የመጻፉ ነገር ለዚህ ጽሁፍ ደራሲ ፈጽ
ም የማይሆን ነገር ነው::

2ኛ/ በላቲን ፊደሎች ላይ የተመሠረተው ኢንተ
ርናሲዮናላዊ ፊደል ተሻሽሎ ለኦሮምኛና ለሌሎችም ቋንቋ
ዎች ሊውል ይችላል::ይህ ፊደል በቀላሉሊጠና ስለሚችል
ና ምልክቶችም ቢደረጉ ከፊደሉ ጋር የሚስማሙ ስለሆኑ:
ባጻጻፍ በኩል ብዙ ችግር አይፈጥርም::ፊደሉ.የሚከተለ
ውን ሊመስል ይችላል:—

ʼ a b c(ቸ) č(ጨ) d ɗ(ዸ) e f g(ገ)
h i j(ጀ) k l m n ñ(ኘ) o p p̣(ጰ)
q(ቀ) r s š(ሸ) t ṭ(ጠ) u w(ወ) y(የ) z(ዘ)

ያናባቢዎችን ምልክቶች በሚመለከተው በኩል /ሀ/አጫጭር አናባቢዎች አንዳሉ ያለምልክት ይጻፋሉ:/ለ/በረጅም አናባቢዎች ላይ ሠረዝ ሲደረግ ይቻላል:/ሐ/ረጅም ሆነው የድምጽ ቀናት ባለባቸው ላይ 'ባር ኔጣ'/^/ለማድረግ ይቻላል:/መ/ቀናት በጆ ባለባቸው ላይ ተንሸ ሠያፍ/-/ ለማስቀመጥ ይቻላል::ይህ ለመጀመር ያህል ሲሆን:ወደፊት የአርሞ ቋንቋ በበለጠ ጥልቀት ከተጠና በኋላ ከነዚህ ምልክቶች ለመቀነስና ጠቀላላ አጻጻፉን የበለጠ ቀለጣፉ ለማድረግ ይቻላል::

የወደፊቱን ኢትዮጵያ አስተዳደግ በምንመለከትበት ጊዜ:አርሞኛን ሆነ ሌሎችንም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በዚህኛው ፊደል መጻፍ ብዙ ጥቅሞችን ሊያስከትል እንደሚችል እንገነዘባለን::ከላይ የጠቀስነው የፊደሉ ቁጥር ማነስና በቀላል መጠናት:በጅም ሆነ በመኪና ጽህፈት ወይገም በአተማት በኩል የሚያስገኘው ቀለጣፉነት:ያውሮፓንም ሆነ ሌሎችን በዓለም በብዙ የተሠራጩትን ቋንቋዎች ለመማር አዲስ ፊደል ማጥናት አለማስፈለጉ:እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የጊዜንና የጉልበትን ቁጠባ ስለሚያስከትሉ: ለሳይገንስ:ለቴክኖሎጂና ለጠቀላላውም ኤኮኖሚያዊ እድገት መፋጠን የሚረዱ ይሆናሉ::በነገራችን ላይ:የሺየትናም ሬቮሉሺናውያን የብዙ ሺህ ዓመታት ታሪክ ያላቸውን ፊደሉቻቸውን ትተው በዚህ መሥፈታቸው:በቻይናና በጃፓንም ጭምር በላቲን ፊደላት ቋንቋዎቻቸውን መጻፍ እንዲለመድ የሚደረገው ስራ ጥረት ለፊደሉ ጠቃሚነት ምስክር ናቸው::

3ኛ/አዲስ ፊደሎችን በማገኛውም ጊዜ ለመፍጠር ይቻላል::ግን እዚህም ከሁለት መንገዶች አንዱን መምረ



ጥ የግድ ይሆናል::ወይ እንደላቲን ፊደሎች አናባቢዎች ያሉትን ዓይነት:ያለበለዚያም እንደአማርኛ አያንዳንዱ ፊደል ድፍንድምጽንና አናባቢን አጣምሮ የያዘበት ፊደል መፍጠር::ይህኛው ዘዴ ባማርኛ ፊደሎች ውስጥ ያሉትን ችግሮች መልስ ስለሚያመጣ የሚመረጥ አይደለም::የመጀመሪያው ዘዴ ከሆነ ደግሞ የላቲን ፊደሎች እያሉ በነርሱው መሠረት ላይ የቆሙ አዲስ ፊደሎች መፍጠር ምንም ያህል ትርጉም ሊኖረው አይችልም::...

እንግዲህ የአርሞኛን አጻጻፍ በሚመለከተው በኩል ያለንን አስተያየት ከዚህ በላይ አሰፈርን::ዋናው የጸሁፋችን አርእስት ይህ ስለሆነ ብዙ ጊዜና ቦታ ለርሱ አዋልን እንጂ:የአርሞ ቋንቋ ሌሎችም ብዙ ችግሮች አሉት::1ኛ/የቋንቋው ሰዋሰው እስከዛሬ በሚገባ ተቀናብሮ:ተሟልቶ አልተሠራም::2ኛ/በልዩልዩ የአርሞ ክፍሎች የሚነገሩትን ክፍለቋንቋዎች የማዋሀድ ሥራ ወደፊት ብዙ ድካምን የሚጠይቅ ነው::እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚቻለው በሕዝቡ መካከል ተገኝቶ ሬቮሉሺናዊ ድርጊት ሲፈጸሙ ነው ብለን እናምናለን::እንደዚያም ሆኖ ችግሮቹ ፈጸመው ከመወገዳቸው በፊት ብዙ ዓመታትን ይጠይቃል::ይሁን እንጂ ከላይ በተሰጠው አሳብ ላይ:ወይንም ተሸሎ በተገኘ አሳብ ላይ:በቶሎ ስምምነት ከተገኘና ማህበራችን በአርሞኛ ጽሁፎችን ማቀረብ ከጀመረ:ይህ እራሱ ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ሁለት ችግሮች የመፍትሄ መንገዱ እንደሚከፍት አይጠረጠርም::

እንደዚህ ነው::የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች ባሁኑ ሰዓት በጨለማ ውስጥ በመኖር ላይ ናቸው::ከዚህም የተ.

ነሣ፡አንቱ ትልቅ ደራሲ እንዳለው፡እ ፣ደአዲስ፡ንጹሕ፡ም
ንም እንዳል ተጻፈበት ገጽ ናቸው፡፡በዚህ ንጹሕ ወረቀት
ላይ ከሁሉ ቆንጆ የሆኑ ሥእሎችን ለምሥራት ይቻላል፡ያ
ለበለዚያም ስሕተት በስሕተት ላይ እየደራረቡ በስርዝና
በድለዝ ገጹን ለማበላሸት ይቻላል፡፡ሬቨሉሽናዊ ንቃትን
በማሳየት ትክክለኛውን መንገድ ማግኘት የኛ ጉዳይ ነው

---

<u>ማስታወሻዎች</u>፡፡

1. በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ዓመ ተት በሙሉ የተሰጡት እን
   ደአውሮፓ አቆጣጠር ነው
2. 'መጣረ ቁሰቁሉ' እንስ መጨፍተ ከኩ ሞፋ ቴፍ ከ
   ኩ ሃራ፡፡አፋን ኦሮሞት፡፡ሄኬ አነሳሞስ ነሲብ፡
   ነምኒ በየ ኦሮሞ፡፡ቀዱስ ክሪሸና 1899
3. Journal of Ethiopian Studies. Vol. VII, No.2, JulY 1969, pp.79 and following.
4. Ibid.
5. A. W. Hodson & C. H. Walker: An Elementary and Practical Grammar of the Galla or Oromo Language. William Clowes & Sons Ltd.,London and Beccles, 1922
6. Ibid. p.7
7. E. Cerulli: The Folk-Literature of the Galla of Southern Abyssinia. Harvard African Studies, Vol.III, 1922
8. M. M. Moreno:Grammatica Teorico-Pratica della Lingua Galla, Roma, 1939



8. Moreno: Favole e Rime Galla Roma, 1935
9. Gaetano da Thiene: Dizionario della Lingua Galla, con brevi nozioni grammaticali, Harar, 1939
10. M. Nordfeldt: A Galla Grammar, in Le Monde Oriental, Vols. 33,34 & 35, 1939,1940, 1941, Uppsala, 1947
11. ኩሻዊ ወይንም ኩሺቲክ የተባለው አጠራር ከመጽሀ
    ፍቅዱሱ ኩሽ ጋር ከስሙ በስተቀር የተጨበጠ የዘ
    ር ወይንም የነገዱ ግንኙነት የለውም፡፡
12. M. L. Bender: The Languages of Ethiopia: A new Lexico-statistic Classification and Some Problems of Diffusion. Anthropological Linguistics, (Anthropology Dept.,Indiana Univ.) Vol. 13, No. 5, May 1971
13. Nordfeldt, p.2

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች

**የመግቢያ መግለጫዎች::**

I. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ብዙ ከመሆናቸው የተነሣ ጥናትን ለማቃለልና ሥነሥርዓታዊ ለማድረግ አንድ ላይ ሊመደቡና ሊጠኑ የሚችሉበትን ዘዴ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል::ስለዚህም የሚቀጥሉትን ያመዳደብ መጠሪያዎች ከቋንቋ ሊቆች ተውሰናል::

1–'ልሣን' የተባለው ቃል የሚከተሉትን ያመለክታል:

ሀ. የታወቀ ያነጋገር ዘይቤዎች — ዘይቤያተልሣን ወይንም ዲያሌክቶች — ሳይኖረው በተናጋሪዎቹ በሙሉ በአንድ ዓይነት የሚነገር ቋንቋ:

ለ. በተናጋሪዎቹ በሙሉ የታወቀ አንድ ቋንቋ ኑሮ ከርሱ ጋር የሚሄዱ በየቦታው የተለያዩ ዘይቤያተልሣን ያለው ቋንቋ:

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ዓይነት 'አፎች' 'ቋንቋ' በሚለው ቃል ለመጥራት ይቻላል::

ሐ. አንዳንድ ጊዜ ከቦታ ወደቦታ ወይንም ከጎሣ ወደጎሣ የሚለያዩ በመካከላቸውም አንድ ሀያል የሆነ አነጋገር የሌለባቸው አፎች ይገኛሉ::አብዛኛውን ጊዜ ተናጋሪዎቹ በሙሉ ሊግባቡ ይችላሉ:አንዳንድ ጊዜ ግን ሊግባቡ አይችሉም::እንደዚህ ያሉትን አፎች 'ተዛማጅ ዘይቤያተልሣን'—ዲያሌክት ክለስተርስ—በሚል ስም ልንጠራቸው እንችላለን::

በለና በሐ ተራ ቁጥሮች ሥር ለተጠቀሱት ዓይነት አፎች እያንዳንዱን ዘይቤልሣን በዝርዝር አስፍረናል:



እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ሶስቱም ዓይነት አፎች እያንዳንዳቸው የመነሻችን መደብ ይሆናሉ::ለምሳሌ ስለአማርኛ ስናወራ በሀ ሥር ስለተጠቀሰው ዓይነት ቋንቋ እንደምናወራ ሊቆጠር ይችላል::ስለኦሮሞ ስናወራ በለ ሥር ስለተጠቀሰው ዓይነት ቋንቋ እንደምናወራ ሊቆጠር ይችላል::ስለጉራግኛ ወይንም ስለኦማቴ አፎች ስናወራ በሐ ተራ ቁጥር ሥር ስለተጠቀሰው ዓይነት አፍ እንደምናወራ ሊቆጠር ይችላል::ነገር ግን ላመዳደባችን ሶስቱንም ዓይነት አፎች እንደእኩል በመቁጠር የመነሻ መደባችን ይሆናሉ::ለዚህ ለመነሻ መደብ ልሣን የሚል ስም እንሰጠዋለን:: —በንግሊዝኛ ቤዝክ ዩኒት::

2– ሕብረልሣናት

አንዳንድ በልዩልዩ ልሣናት መካከል የቋንቋ ዝምድና —የሰዋሰው: የቃላት: የድምጽ: ያገላለጽ ሥነሥርዓት..— ሊኖር ይችላል::እንደዚህ ያሉትን ተዛማጅ ልሣናት አንድ ላይ 'ሕብረልሣናት' በሚባል በሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ መደብን አንድ ላይ እናመጣቸዋለን::በንግሊዝኛ 'ላንጉዌጅ ግሩፕ'::ለምሳሌ ከኢትዮጵያ ልሣናት መካከል በሲዳሞ:በጉዴላ:በከምባታ:በአላባና በቃቤና ቋንቋዎች መካከል የቋንቋ ዝምድና ስላለ በአንድ ላይ የሲዳሞ ሕብረልሣናት በተባለ በሁለተኛ ደረጃ መደብ ውስጥ ተጠቃለዋል::

3– ታላቅ መደበልሣናት —ላርጀር ዩኒት

አንዳንድ ጊዜ በልዩልዩ ሕብረልሣናት መካከል ወይንም በሕብረልሣናትና በንጥል —ከዚህ በታች በ4 ተራ ቁጥር ተመልከት— መካከል የቋንቋ ዝምድና ይኖራል::

እንደዚህ ያሉትን ተዛማጅ ሕብረልሣናትና ንጥልልሣናት
አንድ ላይ ታላቅ መደበልሣናት በተባለ በሶስተኛ ከፍተ
ኛ መደብ አጠቃልለናቸዋል::ለምሳሌ በሲዳሞ ሕብረልሣናት:
በኦሮሞ ንጥልልሣን:በሶማሌ ተዛማጅ ዘይቤያተልሣንና በ
ሌሎችም አፎች መካከል የሰፋሰውና የሌላም ዓይነት የቋ
ንቋ ዝምድና ስላለ የኩሽ ታላቅ መደበልሣናት በተባለ
መደብ ውስጥ ተጠቃለለዋል::

4— ንጥልልሣን — ሲንግል ዩኒት

አንዳንድ ልሣናት:ቋንቋዎች ወይንም ተዛማጅ ዘይቤ
ያተልሣናት:ከሌሎች ጋር አንድ ላይ በታላቅ መደበልሣናት
—ማለት በሶስተኛ ከፍተኛ ደረጃ መደብ— ውስጥ ሊመደቡ
ሲቻሉ:ከነዚህ ከሌሎች ልሣናት ጋር በቂ ዝምድና ስለሌ
ላቸው በሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ መደብ በአንድ ሕብረልሣ
ናት ሊመደቡ አይቻሉም::እንደዚህ ያሉትን ልሣናት ንጥ
ልልሣናት ብለናቸዋል::

5— ንጥልሕብረልሣናት —አይሶሌትድ ላንጉዌጅ ግሩፕ

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአንዳንድ ሕብረልሣናት ውስጥ
ባሉት ልሣናት መካከል ዝምድና እያለ:በሕብረልሣኑ በራ
ሱና በሌሎች ሕብረልሣናት ወይንም ንጥልልሣናት መካከል
ምንም ዓይነት ዝምድና ስለማይኖር በማንኛውም ታላቅ መ
ደብልሣናት ውስጥ ሊመደብ አይቻልም::ይህ ዓይነቱ ሕብ
ረልሣናት ንጥልሕብረልሣናት "የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል::

6— ተመሣሣይ የሌለው ልሣን —አይሶሌትድ ዩኒት

ከሌላ ከማናቸውም ልሣን ጋር ግንኙነት የሌለው ::



II. በኢትዮጵያ የሚነገሩ ቋንቋዎች እስካሁን በሙሉ አ
ልታወቁም::የታወቁትም ደግሞ በሙሉ በሚገባ ተጠንተው
እንደየዝምድናቸው በክፍልበክፍሉ አልተመደቡም::እስከዛ
ሬ ድረስ ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች የተደረጉት ጥናቶች በ
ሙሉ የተከናወኑት በባእድ የቋንቋ መርማሪዎች ነበር::
ከዚህም የተነሣ የቋንቋዎቹ አጠራሮች በሙሉ በትክክል
የተሰጡ አይመስለንም::—ምክንያቱም የባእድ ቋንቋዎች
በኢትዮጵያ የሚታወቁትን አንዳንድ ድምጾች ለመጻፍ ተገ
ቢዎቹ ፊደላት ስለሌላቸው ነው::ለምሳሌ ቀ:ጬ:ፀ:ጠ:
ጰ..ወዘተ.—::ለመለየት የቻልናቸውን ያጠራር ስሕተቶ
ች ለማረም ሞክረን ነበር::ነገርግን ለመለየት ያልቻል
ናቸው ብዙ ያጠራር ስሕተቶች እንደሚኖሩ በማመን አንባ
ቢዎቻችን ስሕተቶቹን ሲለዩ እንደሚያመለክቱን እንለምና
ለን::

III.በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እያንዳንዱን ልሣን ተናጋሪው
ሕዝብ በሚጠራው ስም ለመጥራት ሞክረን ነበር::አንዳን
ድ ጊዜ ግን ተናጋሪው ሕዝብ ቋንቋውንምሆነ ራሱን በም
ን ስም እንደሚጠራ ካለማወቅ የተነሣ:ቋንቋው በሌላ የ
ኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ወይንም በባእድ ጸሀፊዎች ዘንድ
በታወቀው ስም ጠርተነዋል::የስሙ አባባል ባጠራጠረን
ጊዜ በስሙ አጠገብ የጥያቄ ምልክት አስፍረናል::

IV. አንዳንድ እርማቶችና ማሻሻያዎችን ከማድረግ በስተ
ቀር ይህን ጽሁፍ በቀጥታ A. N. Tucker and M. A.
Bryan: "The Non-Bantu Languages of North Eastern
Africa", Published by International African Ins-
titute, Oxford Univ. Press, London, 1956

ከሚለው ጽሁፍ እንደወሰድን ማመልከት አለብን፡፡ጽሁፉ ግን ቀጥታ ትርጉም አይደለም፡፡ሌሎች የተጠቀምንባቸው መጻህፍት በጽሁፉ መጨረሻ ተመልክተዋል፡፡

---

## I. መግቢያ፡፡

በኢትዮጵያ ከሚነገሩት ቋንቋዎች ለጊዜው 95ቱ ታውቀዋል፡፡ወደፊትም ሌሎች እንደሚታወቁ እናምናለን፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቁጥር ምንም እንኳ በጣም መብዛቱ ባይቀርም፡ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኞቹ በአንድነት የቋንቋ አካባቢ ይፈጥራሉ፡፡

ይህም ማለት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በአንድ ላይ ቢታዩ የተወሰኑ የታወቁ ዓይነተኛነቶችን በአንድነት ይዘው በነዚህም ዓይነተኛነቶች ከሌላ ከማንኛውም የዓለም ቋንቋ ቡድን እንደሚለዩ ይታወቃል ማለት ነው፡፡በሌላ አነጋገር በኢትዮጵያ የሚነገሩት ቋንቋዎች አብዛኞቹ በድምጽ/ፎኔቲክስ/፡በሰዋስው፡በመዝገበ ቃላት/ቮካቡላሪ/ በአገላለጽ ሥነሥርዓት አንድ ዓይነት ተመሣሣይነት ቢኖራቸው፡ይህንንም ተመሣሣይነት የሚሰጡዋቸው ዓይነተኛነቶች ኢትዮጵያ ከተባለው የጂኦግራፊ ክልል ውጭ በሚነገር በማንኛውም ቋንቋ ውስጥ አይገኙም ማለት ነው፡፡ስለዚህ ኢትዮጵያ በቋንቋ ሊቃውንት እንደአንድ የቋንቋ አካባቢ ትቆጠራለች፡፡ለምሳሌ ያህል ሌሎች የቋንቋ አካባቢዎች ባልካን/ደቡብ ምሥራቅ አውሮፓ/፡ካውካሱስ፡ደቡብ እስያ /ሕንድ፡ፓኪስታንና ሲሎን ባንድነት/...ወዘተ. ናቸው



በአንድ የቋንቋ አካባቢ ውስጥ ለሚገኙት ልዩልዩ ቋንቋዎች ተመሣሣይነት መነሻ ምክንያቶች ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡/ሀ/ቋንቋዎቹ ከብዙ ምእት ዓመታት አስቀድሞ አንድ ኑረው ከጊዜ ብዛትና ከቦታ መራራቅ፡ከሕዝብ መፍለስና መደባለቅ..ወዘተ. የተነሣ እየተለያዩ በመሄድ በመጨረሻም ልዩልዩ ቋንቋዎች እስከመሆን ይደርሳሉ /ለ/ልዩልዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ሕዝቦች አጠገብለጠገብ ለብዙ ምእት ዓመታት የባሕል የኢኮኖሚና ሕብረሰባዊ ልውውጥ በማድረግ—አብረው በመነገድ፡በመጋባት፡በመተባበር ወይንም አንዱ ሌላውን አሸንፎ በመግዛት..ወዘተ.— ቢኖሩ ቋንቋዎቻቸው በውስጥ እየተቀራረቡ ይሄዳሉ፡፡

የታወቁትን 95 የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በአምስት ታላላቅ ክፍሎች ለመመደብ ይቻላል፡—

1. ተመሣሣይ የሌላቸው ቋንቋዎች
2. መደባቸው ያልታወቀ ቋንቋዎች
3. የኒል /ኒሎቲክ/ ቋንቋዎች
4. ኩሻዊ /ኩሺቲክ/ ቋንቋዎች
5. ሴማዊ /ሰሚቲክ/ ቋንቋዎች

የያንዳንዱን ቋንቋ ክፍል ለማወቅ በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ የተሰጠውን ሠንጠረዥ መመልከት፡፡

## II.

### ተመሣሣይ የሌላቸው ቋንቋዎች

በዚህ ክፍል ሥር እንዲሁም በክፍል ሁለትና ሶስት ሥር የተመደቡት ቋንቋዎች በሙሉ የሚነገሩት በኢትዮጵያና ሱዳን የጠረፍ ክፍሎች፡ከኤርትራ ደቡብምእራብ

ደምር ዙሪያውን እስከሩደልፍ ሀይቅ ድረስ በሚዘልቀው፡ ከኢትዮጵያ የምእራብ ተራሮች ወረድ ብሎ በሚገኘው ረባዳ አገር ነው::

ተመሣሣይ እንደሌሎቻቸው የተቆጠሩት ቋንቋዎች በሰፊው አልተጠኑም::ስለዚህ አመዳደባቸው እስካሁንም ማከራከሩ አልቀረም::በዚህ ክፍል ሥር የተመደቡት ቋንቋዎች የሚከተሉት ናቸው:—

/1/ባሪያ /ቋንቋ/

የባሪያን ቋንቋ የሚናገረው ሕዝብ ባሪያ በሚባል ስም ይጠራል::ይህ ስም ለሕዝቡ የተሰጠው በጎረቤቶቹ በሚኖሩት ሌሎች ሕዝቦች ነው::ሕዝቡ ግን እራሱን በአንድ አጠቃላይ ስም አይጠራም::እያንዳንዱ የሕዝቡ ቀርንጫፍ ራሱን በየጎሣው ስም ይጠራል::

የሚነገርበት ሥፍራ:— በኤርትራ ውስጥ ባረንቱ ከተባለው ከተማ በስተሰሜን:አሚዳብ:መጋረብ:እንዲሁም መረብ በተባሉት ወንዞች ሸለቆዎች ውስጥና በባርካም ወንዝ የግራ ዳርቻ ላይ ነው::ባጭሩ:የባሪያ ቋንቋ የሚነገረው በጋሽና ሰቲት ቆላ አገር በሰሜናዊው ክፍል ነው

/2/ኩናማ /ቋንቋ/

የኩናማን ቋንቋ የሚናገረው ሕዝብ ስሙም ኩናማ ነው::የኩናማ ሕዝብ ባካባቢው በሚኖሩት ሕዝቦች ዘንድ ባዛ ወይም ባዜን በሚል ስም ይጠራል::የኩናማ ሕዝብ የባሪያ ሕዝብ የደቡብ ጎረቤት ነው::

የሚነገርበት ሥፍራ:— በኤርትራ ውስጥ በጋሽና ሰቲት /ተከዜ/ ወንዞች ሸለቆ ባረንቱ ከተባለው ከተማ



በስተደቡብ በሚገኘው ክፍል ውስጥ ነው::በምእራብ በኩል እስከሱዳን ሲዘልቅ:በደቡብ ደግሞ እስከሰሜን ቤገምድር ይዘልቃል::የኩናማ ቋንቋ የተለያዩ ዘይቤዎች እንዳሉት ይነገራል::ሆኖም ይህ ተጣርቶ ያልታወቀ ነገር ነው::

/3/ በርታ /በርጧ/ ቋንቋ /ንጥልልሣን/

የበርታ ተናጋሪዎችና ቋንቋውም በባእድ ጸሀፊዎች ዘንድ በዚሁ ስም ይታወቃሉ::በዓረብኛ ተናጋሪዎች ዘንድ ተናጋሪዎቹ ቤኒሻንጉል በሚል ስም ሲታወቁ: በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ በልዩልዩ ስም ይታወቃሉ::ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ ጥቁር ዓረቦች ይባላሉ::ይህ ዓረብኛም ስለሚናገሩ ነው::የኦሮሞ ሕዝብ ደግሞ ሾገሌ በሚል ስም ሲጠራቸው ይሰማል::

የሚነገርበት ሥፍራ:— በርታ በሱዳንና በኢትዮጵያ ወሰን ላይ በሁለቱም አገሮች ውስጥ ይነገራል::ተናጋሪዎቹ የሚኖሩበት ሥፍራ በስተሰሜን በኩል ከጥቁር ዓባይ መለስ:በስተምእራብ በኩል በሱዳን ውስጥ የኩሩን:የታቢና ኡዱክ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ከሠፈሩበት አገር መለስ:በስተደቡብ በኩል እስከያቡስ ወንዝ ድረስ:በስተምሥራቅ በኩል ምናልባት እስከጥቁርዓባይና ዲዴሣ ወንዞች ይዘልቃል::በሌላ ቦታ ደግሞ የበርታ ተናጋሪዎች በሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪዎች—ለምሳሌ በኮማ ሕዝቦች—መካከል ሠፍረው ይገኛሉ::በኢትዮጵያ ውስጥ የበርታ ተናጋሪዎች አገር በወለጋ ጠቅላይ ግዛትና በሱዳን ወሰን ላይ ሲሆን:የታወቀ የተናጋሪዎች ሥፍራ አሶሳ የተባለው ከተማ

ነው፡፡ የበርታ ተናጋሪዎች ብዛት በኢትዮጵያ ውስጥ አይ
ታወቅም፡በሱዳን ውስጥ ግን እስከ 20000 ይደርስ ይገ
መታል፡፡

የበርታ ልዩልዩ ዘይቤዎች ተጣር ተው አልታወቁም
ነገርግን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከተሉት ዘይቤዎች መኖራ
ቸው ተረጋግጦአል፡፡

— ቀ ኮሾ

— ቀ ዳሺ — ይህ ፋዳሲ ከሚባለው የቦታ ስ
ም ጋር ይመሳሰላል፡የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡

— ሪባቤያ

/4/ ኮማ /ንጥል ሕብረለሣናት/

የኮማ ሕብረለሣናት የሚከተሉትን ቋንቋዎችና ተ
ዛማጅ ዘይቤዎች ያዛሉ፡— ጉሚዝ /ጉሙዝ/ ቋንቋ፡
ኡዱክ ቋንቋ፡ጋንዛ ቋንቋ፡ኮማ ተዛማጅ ዘይቤያተልሣናት፡
ግዋማ ቋንቋ፡ማኦ ቋንቋ፡፡ከነዚህም መካከል ኡዱክና ጋ
ንዛ በኢትዮጵያ ውስጥ አይነገሩም፡፡

—ጉሙዝ /ጉሚዝ/ ቋንቋ

ተናጋሪዎቹ ጉሙዝ /ጉሚዝ/ ይባላሉ፡፡የሚነገር
በት ሥፍራ፡— በሱዳንና በኢትዮጵያ ወሰን ላይ ሲሆን፡
አብዛኛው የጉሙዝ ተናጋሪ የሚኖረው በኢትዮጵያ ውስጥ
ነው፡፡ሕዝቡ የሚኖርበት ሥፍራ በሰሜን በኩል እስከጎን
ዶዋ ወንዝ፡ምናልባትም እስከአንገረብ ወንዝ ይዘልቃል፡፡
በምሥራቅ በኩል እስከየት እንደሚዘልቅ በርግጥ አልታወ
ቀም፡፡በስተደቡብ በኩል የዓባይን ወንዝ ይሻገራል፡፡
በስተምእራብ የሱዳንን ወሰን አቋርጦ ምናልባት እስከ



ፋዘሎ ይዘልቃል፡፡በኢትዮጵያ ውስጥ ጉሙዝ የሚነገርበ
ት አገር አብዛኛው በጎጃምና በቤገምድር ጠቅላይግዛቶች
ምእራባዊ ወሰን ክፍል ውስጥ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

—ኮማ፡ ተዛማጅ ዘይቤያተልሣን

ተናጋሪዎቹ በዓረብና ተናጋሪዎችና በአውሮፓውያ
ን ዘንድ ኮማ በሚባል ስም ይታወቃሉ፡፡የኦሮሞ ሕዝብ
ኮሞ በሚል ስም ይጠራቸዋል፡፡ተናጋሪዎቹ ግን ራሳቸውን
ጉክወም ወይንም ሄይ ሄይ /ሃያሃያ/ በሚል ስም ይጠራሉ
ይባላል፡፡ይህ ግን አልተጣራም፡፡

የሚነገርበት ሥፍራ፡— በኢትዮጵያና በሱዳን ወ
ሰን ላይ በሁለት የተለያዩ ሥፍራዎች ነው፡፡/ሀ/ከያቡ
ስ ወንዝ በስተሰሜን፡/ለ/በስተሰሜን ከጀበል መንጋ አ
ንስቶ በስተደቡብ እስከጂካው ወንዝ ይደርስ ባለው ሥፍራ
መካከል፡፡የኮማ ሊዩልዩ ዘይቤዎች ተጣር ተው አልታወቁም

—ግዋማ /ግዋሚ/ ቋንቋ

ተናጋሪው ሕዝብ በኮማ ሕዝብ ዘንድ ኖካኖካ በ
ሚል ስም፡በበርታ ሕዝብ ዘንድ አማም /ግን ማለትም ተ
መልከት/ በሚል መጠሪያ ይታወቃል፡፡ተናጋሪዎቹ በኮማ
ሕዝብ ውስጥ ተደባልቀው እየኖሩ፡ግን ሌላ ቋንቋ አላቸ
ው ይባላል፡፡

—ማኦ፡/የሰሜን ክፍል/ ቋንቋ

ተናጋሪዎቹ ራሳቸውንም ሆነ ቋንቋቸውን ማኦ በ
ሚል ስም ይጠራሉ፡፡ነገርግን የኮማ ሕዝብ ሲጋዩ ወይን
ም ማዩ በሚል ስም ይጠራቸዋል፡፡ለዓረብኛ ተናጋሪዎች
አማም /ግን ከዚህ በላይ ግዋማ ሥርም ተመልከት/ በሚል

መጠሪያ ይታወቃሉ፡፡ቋንቋው የሚነገርበት ሥፍራ ከላቲቱ
ዱ 9 ዱግሪ ሰሜን በዳቡስ ወንዝ የገራ ዳርቻ ላይ ነው
ማሰሰቢያ፡፡ማኦ የተባሉት ሕዝቦች በሁለት በጣ
ም በሚራራቁ ሥፍራዎች ይኖራሉ፡፡የደቡባዊው ክፍል ሕዝ
ብ ቡጋሴ የተባሉትን፡ምናልባት ከከፋ የመጡ ይሆናሉ ተ
ብለው የሚገመቱትን፡የጎዝዎቹን ቋንቋ ይናገራሉ፡፡ይህ
ቋንቋ ከፊና /ከፋ/ ከተባለው ኩሻዊ ቋንቋ ጋር በጣም
ይቀራረባል፡፡ሰሜናዊው የማኦ ሕዝብ ግን ሌላ ኩሻዊ ቋ
ንቋ ያልሆነ አፍ ይናገራል፡፡ሁለቱም ሕዝቦች ግን ሳ
ቸውን ማኦ በሚል ስም ይጠራሉ፡፡ነገርግን ግልጽ ለመሆ
ን በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ደቡባዊውን የማኦ ሕዝብ አንፊሎ
በሚል ስም እንጠራቸዋለን፡፡ይህ ስም በኦሮሞ ሕዝብና በ
ባእዱ ጸሀፊዎቹም ዘንዱ የተለመደ ነው፡፡

III

መደባቸው ያልታወቀ ቋንቋዎች

በቂ ጥናት ስላልተደረገባቸው የሚከተሉት ቋንቋ
ዎች መደባቸው በርግጥ አልታወቀም፡—

/1/ ገለብ ቋንቋ

የገለብ ቋንቋ ብዙውን ጊዜ በኩሽ ታላቅ መደበ
ለሣናት ውስጥ ይመደብ ነበር፡፡ነገርግን በቅርቡ በተገ
ኘው መረጃ መሠረት ኩሻዊ ቋንቋ አለመሆኑ ተረጋግጦአል
ሆኖም መደቡ ገና አልታወቀም፡፡ተናጋሪው ሕዝብ ራሱን
ዳሳናይክ ወይንም ዳሳኔክ በሚል ስም ይጠራል ይባላል፡
ይህም ገና አልተረጋገጠም፡፡የኢትዮጵያ መንግሥት ገለብ
በሚል ስም ሲያውቃቸው የባእዱ ጸሀፊዎች ደግሞ ማሪሌ



ወይንም ረሺያት በሚል ስም ያውቋቸዋል፡፡

የሚነገርበት ሥፍራ፡— ከሩዶልፍ ሀይቅ በስተሰ
ሜንና በኦሞ ወንዝ ዳርቻ፡ሩዶልፍ ሀይቅ መግቢያው ገደ
ማ ላይ ነው፡፡እንዲሁም በስተደቡብ በኬንያ ውስጥ፡፡

/2/ ኢሌት ቋንቋ

ይህ ቋንቋ የሚነገረው በኤርትራ ውስጥ በቤኒአ
ሚር አገር፡በአልኮታ ጋራዎች ላይ ነው፡፡ተናጋሪዎቹ ከአ
ንዱ ሺህ አይበልጡም፡፡ይህ ቋንቋ ከባሪያም ሆነ ከኩና
ማ ከመለየቱና ኩሻዊ ወይንም ሴማዊ ቋንቋ ካለመሆኑ በ
ስተቀር ምንም አልታወቀም፡፡

ከዚህ በታች የሚጠቀሱት ቋንቋዎች ጊጊንጋ—ሙርሌ
ከተባለው ያፍሪካ ንጥል ሕብረለሣናት ውስጥ አንዱ ላይ
ሊመደቡ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ነገርግን በቂ ጥናት
ስላልተደረገባቸው መደባቸው በርግጥ ተለይቶ አልታወቀም

/3/ ሡሪ /ሹሪ/

ተናጋሪዎቹ ራሳቸውን ሡሪ /ሹሪ/ በሚል ስም
ይጠራሉ፡፡የሚነገርበት ሥፍራ በኢትዮጵያና ሱዳን የደቡ
ብ ወሰን ላይ ከሩዶልፍ ሀይቅ በስተምእራብ የቦማ ኮረ
ብታ/ኘላቶ/ በተባለው ሥፍራ ነው፡፡የተናጋሪዎቹ አገር
እንበርት ኮማ የተባለው በላቲቱዱ 6 እና በሎንጊቱዱ
35 የሚገኘው ቦታ ነው፡፡አብዛኛው ተናጋሪ በሱዳን ው
ስጥ ሲሆን በኢትዮጵያም ጥቂቶች ይኖራሉ፡፡

/4/ መካን /መቃን/

ተናጋሪዎቹ በከፋ ሕዝብ ዘንዱ ሹሮ በሚል ስም

በጊሜራ ሕዝብ ዘንዱ ሱርማ በሚል ስም ይታወቃሉ::
የሚነገርበት ሥፍራ የፈረስ ፋና ቀርጸ ባለውና የማጂን
ሕዝብ ከሌሎው የጊሜራ ተናጋሪ በሚለየው አገር::

/5/ ቴርማ /ቴሪማ/

የመካን ዘይቤ ይሁን ወይንስ ራሱን የቻለ ቋን
ቋ ተለይቶ አልታወቀም:: የሚነገርበት ሥፍራ ከማጂ በስ
ተምእራብ በኪቢሽ ወንዝ ሸለቆ:እንዲሁም በኢትዮጵያና
ሱዳን የደቡብ ወሰን በቴዉና በበሪማ ተራሮች ላይ ነው

/6/ ቴዱ /ቴዲ/

የመካን ዘይቤ ይሁን ራሱን የቻለ ቋንቋ ተለይ
ቶ አልታወቀም:: የሚነገረው ከቴርማ በስተደቡብ በቴዱ
ተራራ ላይ ነው::

/7/ ማሳንጉ ቋንቋ

ተናጋሪዎቹ ራሳቸውን መዠንግር /ማዠንግር/ በ
ሚል ስም ይጠራሉ ይባላል:: አልተረጋገጠም:: የኦሮሞ ሕ
ዝብና የባእዱ ጸሀፊዎች ማሳንጉ በሚል ስም: የሸቃ ሕዝ
ብ ማሻንጉ በሚል ስም ይጠሯአቸዋል:: የሚነገርበት ሥፍ
ራ በስተሰሜን በባሮ ወንዝ:በስተደቡብ በባቆ ወንዝ:በ
ስተምሥራቅ በሸቃ ሕዝብ /ማለት የካፊኖ ተናጋሪዎች/
አገር:በስተምእራብ በአኒዋይ ሕዝብ አገር በታጠረው አ
ገር ውስጥ ነው::ጥቂት ማሷንጉች ከዚህ ሥፍራ በስተሰ
ሜን በጉሬ አቀራቢያ ይኖራሉ::ደግሞም በስተደቡብ ወጣ
ብለው በአኮቦ ወንዝ ዳርቻ ላይ ይገኛሉ::

/8/ ሙርዙ /ሙርሱ:ሙርዚ/

በሶዎና በኦሞና ወንዞች መካከል ይነገራል::



# IV

## የኒል ቋንቋዎች /ታላቅ መደበልሣናት/

ከኒል ቋንቋዎች የሚከተሉት ሁለቱ ብቻ በኢትዮ
ጵያ ውስጥ ይነገራሉ:-

/1/ ኑዌር /ተዛማጅ ዘይቤያተልሣን/

የኑዌር ተናጋሪዎች እስከ 260000 ይደርስ ሲ
ገመቱ አብዛኞቹ የሚኖሩት በሱዳን ውስጥ አፐር ናይል
በተባለው ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ነው::በኢትዮጵያ ውስጥ
በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ሲኖሩ የሚገኙትም በሱዳንና በኢትዮ
ጵያ ወሰን በባሮ ወንዝ ዳርቻ ላይ ነው::በኢትዮጵያ
ውስጥ የሚኖረው የኑዌር ሕዝብ አቢጋር በሚል መጠሪያ
ይታወቃል::በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገረው የኑዌር ዘይቤ
ምሥራቃዊ ጂካኒ የተባለው ነው::በሱዳን ውስጥ የኑዌር
ቋንቋ ለትምህርት ያገለግል ነበር /በእንግሊዝ ቅኝ አገ
ዛዝ ሥር/::በዚህ ቋንቋ የተጻፉ ጥቂት መጻሕፍት አሉ

/2/ አኒዋይ ቋንቋ

ተናጋሪዎቹ ራሳቸውን አኒዋይ /በነጠላ አኒዎአ/
በሚል ስም ይጠራሉ::ባእዱ ጸሀፊዎች አኑዋክ በሚል ስ
ም ሲጠሯዋቸው:በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ያምቦ ይባላሉ::
የሚነገርበት ሥፍራ:- ሀ/ በሱዳን ውስጥ በአኮቦ ወን
ዝ ዳርቻ ላይ ከአኮቦ መንደር እስከ ሳቴቱ 6· ዲግሪ
ከ45 ደቂቃ::ለ/በኢትዮጵያ ውስጥ በአኮቦ ወንዝ የቀ
ኝ ዳርቻ:እንዲሁም በባሮና በባቆ /ጊላ/ ወንዞች ዳር
ቻ ላይ::ከ50000 በላይ ከሚቆጠሩት የአኒዋይ ተናጋ
ሪዎች 40000 የሚኖሩት በኢትዮጵያ ውስጥ ነው::

## V
## ኩሻዊ ቋንቋዎች /ታላቅ መደበለሣናት/

በኢትዮጵያ የሚነገሩት ኩሻዊ ቋንቋዎች እንደሚከተለው ይከፈላሉ:-

ሰሜናዊ ክፍል:- በዳዊዬ /ቤጃ/ ቋንቋ

ማእከላዊ ክፍል:- የአገው ቋንቋዎች /ሕብረ ለሣናት/

ምሥራቃዊ:- ሳሆ-አፋር /ሕብረለሣናት/:
ሲዳሞ /ሕብረለሣናት/
ኦሮሞ /ቋንቋ/
ሶማሌ /ቋንቋ/
ኮንሶ /ቀንጾ/ /ቋንቋ/
ፀማኮ /ቋንቋ/
አርቦሬ /ቋንቋ/

ምእራባዊ:- የማ /ጃንጀሮ/ /ቋንቋ/
ሶማቴ /ሶማቲ/ /ተዛማጅ ዘይቤ ያተለሣን/
ጊሚራ /ቋንቋ/
ካፊኖ /ከፋ/ /ሕብረለሣናት/
አሪ /ባኮ/ /ሕብረለሣናት/

ከነዚህ መካከል የምእራብ ክፍል ኩሻዊ ቋንቋዎች የቋንቋ ሊቃውንት የተስማሙባቸውን የኩሻዊ ቋንቋ ባይነተኝነት በሙሉ አይከተሉም::ማለት ከእውነተኛ ኩሻዊ ቋንቋዎች ባንዳንድ አንጻሮች ይለያሉ ማለት ነው::

ከዚህ በታች እያንዳንዱን ኩሻዊ ቋንቋ በዝርዝር እናመለከታለን:-



/1/ በዳዊዬ /ቤጃ/ / ንጥል ቋንቋ/

ተናጋሪዎች: በዳዊዬ የሚነገረው በቤኒ አመር ና በሌሎችም አንዳንድ የትግሬ ህዝብ ጎሳዎች ነው::

የሚነገርበት ስፍራ: በኤርትራ ውስጥ በአጉርዳት ና በከረን ግዛቶች ውስጥ ነው::በሱዳን ውስጥ በከሰላ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ ይነገራል::

/2/ አገውኛ /ህብረለሳናት/

አገውኛ አንድ ቋንቋ ሳይሆን ህብረለሳናት ነው: የሚከተሉትን ቋንቋዎችና ዘይቤዎችን ያጠቃልላል::

— ቢሊን /ቢሌን/ ቋንቋ
— ኪሚር ተዛማጅ ዘይቤያተለሳን
— ቋራ ቋንቋ
— አዊያ ቋንቋ

ተናጋሪዎች: ከቢሊን ተናጋሪዎች በስተቀር አገውኛን የሚናገሩ ህዝቦች በሙሉ አገው የሚለው ቃል ስማቸው መሆኑን ያውቃታል፤ ይቀበሉታል:: የአገውኛ ቋንቋዎችና ዘይቤዎች እየተረሱ በማደር ላይ ናቸው::አብዛኞቹ የአገው ህዝቦች ትግሬ: ትግርኛ ወይም አማርኛ/እንደሚቀርባቸው/ ይናገራሉ::

— ቢሊን /ቢሌን/ ቋንቋ

ተናጋሪዎች: ራሳቸውን ቢሊን ወይም ቦጎስ በሚል ስም ይጠራሉ::የዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች እስከ 30000 ይገመታሉ::ከሌሎች የአገውኛ ተናጋሪዎች ከመራቃቸው የተነሳ ቋንቋቸው ከሌሎች የአገው ቋንቋዎች ለየት ያለ ነው::

በሁለቱ የቢሌን ጉሣዎች/ቤት ታውቄና ቤት ታርቄ/ አነጋገር መካከል የዘይቤ ልዩነት መኖሩ ይነገራል::

የሚነገርበት ሥፍራ:- በኤርትራ ውስጥ በከረን ግዛት::

-ሽሚር /ተዛማጅ ዘይቤያተልሣናት/

ይህ ዘይቤያተልሣን ሽሚርና ኻምታ የተባሉትን ዘይቤዎች ያጠቃልላል::

-ሽሚር በትግሬ ጠቅላይግዛት /አሸርገሌ/ በተባለ አካባቢ ይነገራል::ይህ ዘይቤ ለትግርኛ ቦታ እየለቀቀ ይሄዳል::

-ኻምታ በዋግና በላስታ ግዛቶች የሚነገር ዘይቤ ነው::

- ቋራ /ቋንቋ/

ይህ ቋንቋ የሚከተሉትን ዘይቤዎች ይለያል::

-ቋራ::ይህ ዘይቤ የሚነገረው በጣና ሀይቅ የምእራብ ዳርቻ ላይ ነው::

-ቀማንት::በጣና ሀይቅ የሰሜን ዳርቻ ላይ የሚነገር ዘይቤ ነው::

-ካይላ::በቀማንት ውስጥ የሚገኙት ፈላሻዎች የሚናገሩት ዘይቤ ነው::

-አዊያ /ቋንቋ/

ይህ ቋንቋ የሚነገረው በጐጃም ጠቅላይግዛት አገውምድር በተባለው ሥፍራ ነው::

/3/ አፋር-ሳሆ /ሕብረልሣናት/



ይህ ሕብረልሣናት ስሙ እንደሚያመለክተው በጣም የተቀራረቡ ሁለት ቋንቋዎችን ያጠቃልላል::

-ሳሆ ቋንቋ

ተናጋሪዎቹ: የሳሆን ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ራሱን ሳሆ በሚል መጠርያ ሲያመለክት: የትግረው ህዝብ ሺሆ በሚል ስም ይጠራዋል::

የሚነገርበት ስፍራ: በገሚስ አከለጉዛይና በደቡብ ምጽዋ ግዛቶች: እንዲሁም በአጋሜ ውስጥ እንደ ኢሮግና ሰረኮ ቀበሌዎች ባሉ በተነጣጠሉ ስፍራዎች:: ተናጋሪዎቹ እስከ 50000 ይገመታሉ::

-አፋር /ቋንቋ/

ተናጋሪዎቹ: ራሳቸውን አፋር በሚል ስም ሲጠሩ የኦሮሞው ህዝብ ደንከሌ በሚል ስም: ያማራው ህዝብ አዳል በሚል ስም: የትግሬው ህዝብ ጠልጠል በሚል ስም: ኢውሮፓውያንና አረቦች ደናኪል በሚል ስም ያውቋቸዋል::

የሚነገርበት ስፍራ: ከምስራቅ ደቡብ ኤርትራ እስከምእራብ የፈረንሳይ ቀኝ ግዛት ድረስ ከዚያም በስተምእራብ በአዋሽ ሸለቆ ውስጥ እስከመተሀራ ድረስ: እንዲሁም በዳህላቅ ደሴቶች ውስጥ ይነገራል::ቋንቋው የሚነገረው በሪፍት ሸለቆ /ስምጥ ሸለቆ/ የሰሜን አጋማሽ ውስጥ ነው ለማለት ይቻላል::

/4/ ሲዳሞ /ህብረልሳናት/

የሚከተሉትን ቋንቋዎችና ዘይቤዎች ይይዛል::ጉዴላ:/ሀዲያ/ ቋንቋ: አላባ ቋንቋ: ከምባታ ተዛማጅ ዘይቤያተልሳን: ቃቤና:ሲዳሞ ቋንቋ:ደራሳ ቋንቋ: ምናልባት ባንባላ ቋንቋ::

ሲዳሞ የሚለው ቃል ለጊዜው በጣም አሳሳች ነው እንደደንቡ ሲሆኑ ቃሉ የአንድ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኝ ህዝብ ስም ነው:: ነገር ግን የኦሮሞ ህዝብ በዚያ አካባቢ የሚገኘውን ኦሮሞ ያልሆነ ህዝብ በሙሉ ሲዳሞ/ሲዳማ/በሚል ስም ይጠራ ነበር:: የባእድ ጸሀፊዎችም ወደኢትዮጵያ ደቡብ በመጡ ጊዜ ይህን ስም በመውሰድ ኦሮሞ ያልሆነውን የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ /ከፋ: ዳንጀር: ጊሚራ: ኦመቴ: ኮንሶ .....ወዘተ./ ሲዳማ በሚል ስም: ቋንቋውንም ሲዳሞ በማለት በየጽሁፎቻቸው አመለከቱ:: በኢጣሊያን ቀኝ አገዛዝ ጊዜ ደቡብ ኢትዮጵያ ጋላ—ሲዳማ በሚል ግዛት ስር ይተዳደር ነበር:: ዛሬም ሲዳሞ የሚባል በዙ ህዝብን አቀፍ የሆነ ጠቅላይ ግዛት እንዳለ እናውቃለን::

ስለዚህ ግልጸ ለመሆን ያህል ሲዳሞ የተባለው ህብረልባናት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሰባት ቋንቋዎች ብቻ የሚያመለክት መሆኑን ማስታወስ አለብን:: የሲዳሞ ቋንቋ ስንል የእውነተኛው የሲዳሞ ህዝብ /ማለት ራሱን ሲዳሞ ብሎ የሚጠራውን ህዝብ /ቋንቋ ማመልከታችን መሆኑ መታወቅ ይገባዋል::

— ጉዴላ/ሀዲያ/ ቋንቋ

የጉዴላ ህዝብና ቋንቋ ሀዲያ በሚል ስም ይታወቃል:: ህዝቡ ግን ራሱን ጉዴላ በሚል ስም ይጠራል:: የሚነገርበት ሰፍራ: በኦሞና በቢላቴ ወንዞች መካከል ከጉራጌ አገር በስተምእራብ ነው::

— ከምባታ / ተመሳሳይ ዘይቤያተሰባን/



ይህ ዘይቤያተልሣን የከምባታንና የጣምባሮን /ፃምባሮ/ ዘይቤዎችን ያጠቃልላል::

—ከምባታ ዘይቤ: የሚነገረው ከምባታ በተባለው ሕዝብ ሲሆን: የሚነገርበት ሥፍራ ከጉዴላ በስተደቡብ ነው

—ጣምባሮ /ፃምባሮ/ የሚነገረው በጣምባሮ ሕዝብ:: የሚነገርበት ሥፍራ ከከምባታ በስተደቡብ::

—አላባ ቋንቋ:: ተናጋሪዎቹ አላባ ይባላሉ:: የሚነገርበት ሥፍራ የጣምባሮ ዘይቤ ከሚነገርበት በስተምሥራቅ: በቢላቴ ወንዝ የግራ ዳርቻ እንዲሁም በወንዙና በአዋሽ ሸለቆ መካከል ነው:: የአላባ ተናጋሪዎች አገር አንብርት ቁሊቶ የተባለ ቦታ ነው::

—ሲዳሞ ቋንቋ:: ተናጋሪው ሕዝብ ሲዳማ ይባላል የሚነገርበት ሥፍራ: ወደዋቢ ሸበሌና ጁባ ሸለቆች የሚፈሰውን ውሀ ወደአቦያ ሀይቅ ከሚፈሰው ውሀ የሚለዩ ተራሮች /ወተርሸድ/ ላይ ነው:: በስተምሥራቅ እስከገናሌ ወንዝ ድረስ: በስተምእራብ እስከአቦያ ሀይቅ: በስተሰሜን እስከአዋሳ ሀይቅ ይዘልቃል::

—ደራሳ ቋንቋ:: ተናጋሪው ሕዝብ ደራሳ ይባላል የሚነገርበት ሥፍራ ከሲዳሞ በስተደቡብ:/ቀቤና/ ከጉራጌ አገር በስተሰሜን ካዲስአበባ በስተደቡብ ባለው ቀቤና በተባለው ሥፍራ በጥቂት ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ የሚናገረው ቋንቋ ነው:: ይህ ቋንቋ በሚነገርበት ሥፍራና ሌሎች የሲዳሞ ቋንቋዎች በሚነገሩበት ሥፍራ መካከል የጉራጌ አገር ይገኛል::

—ባምባላ /ቡርጂ/ ቋንቋ:: ተናጋሪዎቹ ባምባላ

ይባላሉ:: የኦሮሞ ህዝብ አማሮ በሚል ስም ይጠራቸዋል::
ከኢትዮጵያ ውጭ የሚታወቁት ቡርጂ በሚል ስም ነው::አ
ንደደንቡ ሲሆን ቡርጂ የሚለው ስም ህዝቡ በሚኖርበት
ስፍራ የሚገኝ የተራራ ስም ነው:: የሚነገርበት ስፍራ
በቡርጂ ተራራ አካባቢ: ከጫሞ ሀይቅ በስተደቡብ ነው::
ማለት በስተምስራቅ በሳጋን ወንዝ: በስተደቡብ በቢሻን
ጉራቻ /ጥቁር.ውሀ/መካከል ባለው ስፍራ ነው::

/5/ የኦሮሞ ቋንቋ /ንጥል ቋንቋ/

ተናጋሪዎቹ ራሳቸውን ኦሮሞ በሚል ስም ሲጠሩ:
በሌላው ህዝብ ዘንድ ጋላ በሚል ስም ይታወቃሉ:: የሚነ
ገርበት ስፍራ:— በስተሰሜን ከአባይ ወንዝ በስተደቡብ
አስከጉጀብ ወንዝ ባለው የኢትዮጵያ ምአራባዊ ተራሮች
ክፍል:በሸዋ ጠቅላይግዛት ገሚስ:በወሎ ጠቅላይግዛት ገ
ሚስ:በጉራጌ:ሲዳሞ:ደራሳና ሶማሌ ተናጋሪዎች አገር በ
ተከበበው ሥፍራ በሙሉ:ከገላና ሳጋን ወንዝ እስከጨው
ባሕር:ከገላፍ ደሪያ ሸለቆ አንስቶ እስከኬንያ ጠረፍ
ባለው ሥፍራ::ከዚህም ሌላ በኬንያ ውስጥ በሰሜን የወ
ሰን ጠቅላይግዛቶች/ኖርዘርን ፍሮንትየር ፕሮቪንስስ/
ውስ':እንዲሁም ወረዱ ብሉ በስተደቡብ በሚገኘው የታና
ወንዝ ዳርቻ ላይ ይነገራል::

ኦሮምኛ አያሌ ዘዬዎች እንዳሉት ይታወቃል::
ግን እነዚህ በደንብ ተጠንተው አልተመዘገቡም::ለጊዜው
የሚከተሉትን ዘዬዎች ለማመልከት ይቻላል::

—ማጫ:: የሚነገረው በምአራብ የኦሮሞ ተናጋሪዎ
ች አገር:ከግቤ ወንዝ በስተምአራብ እስከሱዳን ወሰን::



—ቱለማ::ከግቤ ወንዝ በስተምሥራቅ:በሸዋ::

—ኢቱና አሩሲ::በጨርጨር ተራሮች:እንዲሁም በ
አዋሽ ሸለቆ:በዋቢሸበሌና በገናሌ ደሪያ ወንዞች በታጠ
ረው አገር::

—ቦረና::በኢትዮጵያ ውስጥ ከሀይቆቹ በስተደቡ
ብ በሚገኘው አገር:እንዲሁም በኬንያ ውስጥ::

—ዋርዳይ::በኬንያ የሰሜን ወሰን ግዛቶች::

/6/ሶማሌ /ሶማሊ/ ቋንቋ /ንጥልልሣን/

ተናጋሪዎቹ በራሳቸውም ሆነ በሌላው ሕዝብ ዘን
ዱ ሶማሊ በሚል ስም ይታወቃሉ:: የሚነገርበት ሥፍራ:—
በጂቡቲ የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ገሚስ:በኢትዮጵያ ውስጥ
በኦጋዴን አውራጃ:በሶማሊያ ሬፑብሊክ በሙሉ:እንዲሁም
በኬንያ የሰሜን ወሰን ግዛቶች:እንዲሁም በታና ወንዝ
ዳርቻ::

ሶማልኛ ሶስት ታላላቅ ዘዬዎች ሲኖሩት:ሶስቱ
ም እንደገና በንኡስ ክፍሎች ይከፈላሉ::ሶስቱ አቢይ
ዘዬዎች የሚከተሉት ናቸው::

—አንደኛው ዘዬ በሚከተሉት ጎሣዎች የሚነገር
ነው::ኢስዓቅ /ኢስሀቅ/:ዳሮድ:ኢሳ:ጋዳቡርሲ /እነዚ
ህ ሁለቱ አንድነት ዲር በሚል ስም ይታወቃሉ/: ሀዊያ

ይህ ዘዬ በሶማሌ አገር በአብዛኛው ቦታ ይነ
ገራል::እንደዚሁም በፈረንሣይ የጂቡቲ ቅኝግዛት:በሶማ
ሊያ ሬፑብሊክ ያሰሜን ክፍል:በኢትዮጵያና በኬንያ::

—ሁለተኛው ዘዬ ራሃንዌይን በተባለው ጎሣ የ
ሚነገር ነው:: የሚነገርበት ሥፍራ በማአከላዊና በደቡባ

ዊ ሶማሊያ ነው:: ነገርግን በሶማሊያ የመጨረሻ የደቡብ ጫፍ የሚነገረው ዘይቤ ከላይ የተጠቀሰው አንደኛው ነው

—ሶስተኛው ዘይቤ:ባንዓዲር:በሶማሊያ የወደብ ከተሞች በሚኖረው ከየጉሣው በተቋረጠውና በተደበላለቀው ሕዝብ የሚነገር ነው::ይህ ዘይቤ በአንደኛውና በሁለተኛው ዘይቤዎች መካከል የሚቆም ነው::

/7/ ኮንሶ /ቀንጾ/ ቋንቋ

ይህ በደንብ ያልተጠና ቋንቋ ነው:: ነገርግን የምሥራቅ ኩሻዊ ቋንቋ መሆኑ ይታመናል:: ተናጋሪዎቹ ቡሳ ገደሌ:ማሺሌ:ጋቶና:ኮንሶ /ቀንጾ/ የተባሉ ጉሣዎች ናቸው:: የሚነገርበት ሥፍራ:ከጫሞ ሀይቅ በስተደቡብ:በባምባሳ:በፂማኮ ተናጋሪዎችና በቦረና ኦሮሞ አገር መካከል ባለው ከወደሥራ ረጅም መያዣ ያለው አንሥራ የመሰለ ቀርጽ ባለው ሥፍራ ነው::

—/8/ ፂማኮ ቋንቋ

ይህኛውም በደንብ ያልተጠና ቋንቋ ነው::ራሱን የቻለ የምሥራቅ ኩሻዊ ቋንቋ መሆኑ ይታመናል::ፂማኮን የሚናገሩ የሚከተሉት ጉሣዎች ናቸው:—ጉዋዜ:ኦርሴ:ታማታይ:ኢጊኔ:ጉላንጉ:ጉራዜ:ጋዋዳ:ጉራ:ፂማኮ:: የሚነገርበት ሥፍራ በስተሰሜን በኦማቴ ተናጋሪዎች:በስተምሥራቅ በኮንሶ ተናጋሪዎች:በስተምእራብ በሀመር ተናጋሪዎች አገር በተከበበው ሥፍራ::

—/9/ አርቦሬ ቋንቋ

ከኦሮሞ ጋር በጣም የሚቀራረብ ቋንቋ ነው:: ለኦሮሞ በታ እየለቀቀ መሄዱም ይታመናል:: ተናጋሪዎቹ



አርቦሬ ይባላሉ:: የሚነገርበት ሥፍራ ከጨው ባህር በስተሰሜን ባለው ቆላ አገር::/ደጋው አገር የተያዘው በሀመር ሕዝብ ነው::/

/10/ የማ /ጃንጀሮ/ ቋንቋ /ንጥልልሣን/

ተናጋሪው ሕዝብ ራሱን የማ በሚል ስም ይጠራል በሌላው ሕዝብ ዘንዱ ጃንጀሮ በሚል ስም ይታወቃል:: የሚነገርበት ሥፍራ በጊቤ ወንዝና በኦሞ ጅረት /ወደመነሻው ግድም/ መካከል ነው::

በየማ ሁለት ልዩ /ተጨማሪ/ የአክብሮት ቋንቋዎች ይነገራሉ::አንዱ ለቤተመንግሥት ብቻ የሚያገለግል ሲሆን:ሁለተኛው ደግሞ ለሌሎች የፊውዳል ባለባቶች የሚያገለግል ነው::በነዚህ ልዩ የአክብሮት ቋንቋዎች ውስጥ የሚገኙ ቃላት ብዙዎቹ ለተራው ሕዝብ በሚያገለግለው ቋንቋ ውስጥ አይገኙም::

/11/ ኦማቴ /ኦሜቴ/ /ሕብረለሣናት/

የኦማቴ አፍ የሚከተሉትን ተዛማጅ የዘይቤዎች ቡድኖች ያጠቃልላል::

ሰሜናዊ ዘይቤዎች: ወላሞ:ዛላ:ጉፋ

ምእራባዊ ዘይቤዎች: ጫራ:ባስኬቶ:

ደቡባዊ ዘይቤዎች: ኮይራ:ቋጫ:ዛይሴ

ኦማቴን ከሚናገረው ሕዝብ መካከል በዚህ ስም ራሱን የሚጠራው የኩሎ ሕዝብ ብቻ ነው:: የተረፈው የኦማቴ ተናጋሪ ራሱን የሚጠራው በሌሎች የጉሣ ስሞች /ለምሳሌ: ወላሞ:ኮይራ:ቋጫ:ጉፋ...ወዘተ/ ነው::

ኦማቴ የሚነገርበት ሥፍራ በስም ወንዝ ማእከላዊ ሸለቆ
ውስጥ ነው፡፡ኦማቴ ማለት የስም ሰዎች ማለት ነው፡፡
ስስቱ የዘይቤ ቡድኖች የሚነገሩባቸው ሥፍራዎች የሚከተ
ሉት ናቸው፡—

—ሰሜናዊ፡፡ወላም የሚነገርበት ሥፍራ በስም ጅ
ረት የገራ ዳርቻና በቤሳቴ ወንዝ መካከል ነው፡፡

—ዛላ የሚነገረው በዛላ ሕዝብ፡፡የሚነገርበት ሥ
ፍራ ከወላም ደቡብምእራብ

—ጎፋ የሚነገረው በጎፋ ሕዝብ፡፡የሚነገርበት ሥ
ፍራ ከዛላ በስተደቡብ፡፡

—ምእራባዊ፡፡ጨራ የሚነገረው በጨራ ሕዝብ፤ የሚነ
ገርበት ሥፍራ ከከፋ በስተደቡብ ባለው የስም ጅረት ዳ
ርቻ ላይ፡፡ባስኬቶ የሚነገረው በባስኬቶ ሕዝብ፡፡ የሚነ
ገርበት ሥፍራ ከጨራ በስተደቡብ

—ደቡባዊ፡፡ኮይራ፡ ተናጋሪው ሕዝብ ራሱን ኮይራ
በሚል ስም ይጠራል፡፡የኦሮሞ ሕዝብ ባዲቶ በሚል ስም
ይጠራዋል፡፡ከኢትዮጵያም ውጭ ባዲቶ በሚል ስም ይታወቃ
ል፡፡የሚነገርበት ሥፍራ ከአባያ ሀይቅ በስተደቡብ፡ከጫ
ሞ ሀይቅ በስተምሥራቅ፡፡ ቋጨማ፡ ተናጋሪው ሕዝብ ራ
ሱን ቋጨማ በሚል ስም ሲጠራ በሌላው ሕዝብ ዘንዱ ሀሩ
ሮ /አሩሮ/ ወይንም ጋዳምባ በሚል ስም ይታወቃል፡፡ የ
ሚነገርበት ሥፍራ፡ ሕዝቡ በአባያ ሀይቅ ደሴቶች ላይ
ዓሣ እያጠመደ ይኖራል፡፡ ዛይሴ፡ ተናጋሪው ሕዝብ ዛ
ይሴ፡ዘይቤው የሚነገርበት ሥፍራ ከጫሞ ሀይቅ በስተደቡ
ብ ዛይሴ በተባለው ሥፍራ ነው፡፡



ብዙ ጸሀፊዎች ሌሎች ብዙ ስሞችን የኦማቴ ዘይ
ቤዎች ናቸው በማለት ይሰጧሉ፡፡ነገርግን እነዚህ ስሞች
አብዛኞቹ የጎሣ ወይም የቦታ ስሞች ናቸው፡፡እላይ ከተ
ጠቀሱት ዘይቤዎች ከወጡ ከሌሎች ዘይቤዎች ጋር ግንኙነ
ት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ሰፊ ጥናት ያስፈልጋል፡፡ለም
ሳሌ ያህል ተደጋግመው ከሚሰጡት ስሞች አንዳንዶቹን እ
ንጠቅሳለን፡፡—

ኦባ፡ ያንዱ ተራራና ያካባቢው ስም፡፡ኩሉ፡ የቦታ
ስም፡፡ሕዝቡ ራሱን ኦማቴ /ኦሜቲ/ በሚል ስም ይጠራል
ዳዋሮ፡ የኩሉ ሌላ ስም፡፡/ይህ ስም በጥንት ዘመን በም
ሥራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው የዳዋሮ መንግሥት ስም
ጋር አንዱ ቢሆንም ቦታዎቹ የተለያዩ ናቸው፡፡/
ወራጨ፡በኩሉ ውስጥ የሚገኝ ጎሣ ነው፡፡ቦንታ፡ማሉ፡ዶኮ፡
የጎሣዎች ስሞች፡፡ ቁጫ /ኩሻ/፡በርዳ፡ገሙ፡ የቦታዎች ስ
ም፡፡

ኦማቴ ምንም እንኳን ከቦታ ወደቦታ እንዲሁም
ከጎሣ የሚለያዩና ከመካከላቸውም አንዱ አያል የሆነ የ
ሌለባቸውን ዘይቤዎች የሚያዘል 'ቋንቋ' ቢሆን ቋንቋው
በመሠረቱ በቃላትም ሆነ በሰዋሰው አንዱ መሆኑን ቋንቋ
ውን ያጠኑ ሰዎች አመልክተዋል፡፡

/12/ አሪ /ባኩ/ /ሕብረልሣናት/

ይህ በደንብ ያልተጠና ሕብረልሣናት የሚከተሉትን
ቋንቋዎች ያጠቃልላል፡፡አሪ/ባኩ/ ቋንቋ፡፡ዲሜ ቋንቋ፡፡
ሀመር ቋንቋ፡፡

ከዚህ በፊት ይህ ህብረለሳናት ተመሳሳይ ከሌላ
ቸው ቋንቋዎች ጋር ይመደብ ነበር::ነገር ግን በቅርብ
በተገኘው መረጃ መሰረት የምእራባዊ ኩሽ ክፍል መሆኑ
ተረጋግጦአል::እያንዳንዱ የህብረ ለሳናት ቋንቋ የሚነገ
ርበት ስፍራ እንደሚከተለው ነው::

አሪ/ባኮ/: ተናጋሪዎቹ ራሳቸውን አሪ በሚል ስ
ም ሲጠሩ: ለውጭው ህዝብ የሚታወቁት ባኮ በሚለው ስም
ነው::የሚነገርበት ስፍራ በኦሞና ወንዝ የምስራቅ ዳር
ቻ ነው:: ዲሜ: የሚነገረው ዲሜ በሚባለው ህዝብ ሲ
ሆን የሚነገርበት ስፍ/ ኦሞና ወንዝ ማእከላዊ ዳርቻ ነው::
ሀመር: የሚነገረው ሀመር:ባሻዳ: ካሮ: ባና በሚባሉ
ጎሳዎች ሲሆን የሚነገርበት ስፍራ ከአሪ በስተደቡብ ነው::

/13/ጊሚራ

ህብረለሳን ወይም ለሳን መሆኑ አልተለየም::ጊ
ሚራ የጊሚራን ዘይቤያተ ለሳናትንና ማጂን ያጠቃልላል::
ማጂ የጊሚራ ዘይቤ ይሁን እራሱን የቻለ ቋንቋ መሆኑ
አልተጣራም::

ጊሚራ የሚለውን ስም ለዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች
በመጀመርያ የተጠቀሙበት ኦሮሞዎች ነበሩ::ዛሬ ህዝቡ
ከኢትዮጵያ ውጭም ሆነ ውስጥ ጊሚራ በሚል ስም ይታወቃ
ል::ህዝቡ ግን ራሱን በየጎሳው ስም ይጠራል እንጂ ባ
ጠቃላይ ስም አይጠቀምም::የሚነገርበት ስፍራ በስተምእ
ራብ ከጉራ ፈርዳ ተራራዎች አንስቶ በስተምስራቅ እስከ
ጧራ አገር በሚዘልቅ: ከሸቃና ከካፊቾ አገር በስተደቡ



ብ በሚገኘው የፈረስ ኮቴ በሚመስል ቅርጽ ባለው ቦታ
ነው::የጊሚራ ልዩልዩ ዘይቤዎች የሚከተሉት ናቸው::

ምእራባዊ: ሻኮ: በጉራ ፈርዳ ተራራዎች ላይ
የሚነገር::

ማእከላዊ: ቤኒሽ: ሺ/ዲዙ/: ካባ::

ምስራቃዊ: ናኦ::

ማጂ /ዘይቤያተ ለሳን ወይም ቋንቋ/ ተናጋሪዎ
ቹ ራሳቸውን ማጂ /ማዢ/ በሚል ስም ይጠራሉ::የሚነገ
ርበት ስፍራ ከጊሚራ በስተደቡብ በሚገኙና ከጊሚራ ተና
ጋሪዎች አገር በሱሪ ተናጋሪዎች አገር በተለየው: የቻ
ካል ቅርጽ ባለው ስፍራ::

/14/ካፊኖ /ህብረለሳናት/

የካፊኖ ህብረለሳናት የሚከተሉትን ያጠቃልላል::
ከፊኖ ዘይቤያተለሳን: ቦሮ/ሺናሻ/ ቋንቋ ወይም ዘይ
ቤያተለሳን መሆኑ አልተለየም::እንፊሎ/ማኦ/ ቋንቋ::

የካፊኖ ዘይቤያተለሳን እንደገና በሚከተሉት ዘ
ይቤዎች ይከፈላሉ::ካፊኖ /ካፋ/ ዘይቤ: ቦሻ/ጋሮ/
ዘይቤ: ሸቃ /ሞቻ/ ዘይቤ::የካፊኖ ተናጋሪ ህዝብ ቋ
ንቋውን ካፊኖ በሚል ስም: ሰውን ካፊቾ /እንስታይ ከ
ፊቼ/ በሚል ስም ይጠራል::የጊሚራ ህዝብ ጎማሮ: ሌላ
ው ህዝብ ካፋ ይላቸዋል::ዘይቤው የሚነገርበት ስፍራ
በኦሞና በጎጀብ ወንዞች መካከል::

ቦሻ ተናጋሪዎች ራሳቸውን ቦሻ ይላሉ::ሌሎች

ሕዝቦች ጋር በሚል ስም ይጠሯሳቸዋል::ዘይቤው የሚነገ
ርበት ሥፍራ ከጎጀብ ወንዝ በስተሰሜን:ከኦሞ ምእራብ::

ሸቃ:: ተናጋሪው ሕዝብ ራሱን ሸቃ በሚል ስም
ሲጠራ:የኦሮሞ ሕዝብ ሞቻ ይሏቸዋል::ባእድ ጸሀፊዎችም
ይህንን ስም ተውሰውታል::ዘይቤው የሚነገርበት ሥፍራ
ከካፋና በስተምእራብ በባሮ ወንዝ ቀኝና ግራ::

ቡዋሮ /ሹናሻ/ ቋንቋ:: ተናጋሪዎቹ ራሳቸውን
ቡዋሮ /ቧሮ/ በሚል ስም ሲጠሩ:በሌላው ሕዝብ ዘንድ
ሺናሻ በሚል ስም ይታወቃሉ:: የሚነገርበት ሥፍራ ከከፋ
ና ሕብረልሣናት ተናጋሪዎች በሙሉ ራቅ ብሎ በስተሰሜን
በአራት ቦታዎች:— በአባይ ሸለቆ:ጉባ በተባለው ከተማ
አካባቢ ማለት በጉሙዝ ተናጋሪዎች መካከል:በወንበራ ደ
ቡብ በኦሮሞ ተናጋሪዎች መካከል ከላቲቱድ 10 ዲግሪ
ከ30 ደቂቃ ሰሜን እንዲሁም በዚሁ ላቲቱድ በስተምሥራ
ቅ በደቡብ አገውምድር ውስጥ ነጋ በተባሉ የጉሙዝ ተና
ጋሪዎች መካከል:በስተደቡብ ወረዳ ብሎ ከአባይ የግራ
ዳርቻ ላይ::

አንፊሎ::/ማኦ የደቡብ ክፍል/ ቋንቋ:: ተናጋ
ሪዎቹ ራሳቸውን ማኦ በሚል ስም ይጠራሉ::ነገርግን ከ
ሰሜናዊ ማኦ ጋር እንዳይቃወስ አንፊሎ በሚል ስም ጠር
ተናቸዋል::/ቀደም ብሎ ስለማኦ የተሰጠውን ማስታወሻ
ተመልከት::/ የሚነገርበት ሥፍራ በአንፊሎ ደን ውስጥ
ከባሮ ወንዝ በስተሰሜን::





## የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች /ታሳቅ መደበለባናት/

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገሩት የሴም ቋንቋዎች
የሚከተሉት ናቸው:: /1/ግእዝ ቋንቋ /2/ትግረ ቋን
ቋ /3/ትግርኛ ቋንቋ /4/አማርኛ ቋንቋ /5/አደርኛ
ቋንቋ /6/አርጎባ ቋንቋ /7/ጉራግኛ ተዛማጅ ዘይቤያ
ተ ለሳን /8/ጋፋት ቋንቋ::

የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች በቋንቋ ሊቃውንት አ
ንደዝምድና ቸው በሁለት ቦታ ተከፍለዋል::በዚህ መሰረት
አሳይ ከተጠቀሱት የመጀመርያ ስስት ቋንቋዎች አንዱ ሳ
ይ ሲሄዱ:የተረፉት አምስት ቋንቋዎችም እንዲሁ አንዱ
ላይ ይሄዳሉ:: የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች በባእድ ጸሀ
ፊዎች ዘንድ በአንድነት 'ኢትዮፒክስ' በሚል መጠርያ
ይታወቃሉ:: ከነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ ትግረ በኢትዮጵያ
ብቻ ሳይወሰን በሱዳንም ውስጥ ይነገራል::

/1/ግእዝ: ይህ ቋንቋ በህዝቡ ዘንድ መነገሩ
ከቆመ ብዙ መቶ አመታት አልፏአል::ነገር ግን በኢትዮ
ጵያ ኦርቶደክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለጸሎትና ለስብከት
ያገለግላል::በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ የሀይማኖትና የታሪ
ክ መጽሀፍቾ በብዛት ይገኛሉ::

/2/ትግረ: ከግእዝ ጋር በጣም የሚቀራረብ ቋ
ንቋ ነው:: ተናጋሪው ህዝብ ስሙም ትግረ ነው::ከትግረ
ህዝብ ውስጥ ቤኒ አሚር የሚባለው ጉባ በቋንቋ አነጋር
በኩል በስስት ቦታ ሊመደብ ይቻላል::ሴቦው ትግረ ሴና

ገር፡ሴሰው በዳዉዴን /ቤጃን/፡ የቀረው ደግሞ ትግረንና
በዳዊዴን /ሁለቱንም/ አጣምሮ ይናገራል፡፡ የትግረ ቋን
ቋ የሚነገርበት ሥፍራ፡በአጐርዳት፡በከረንና በምጽዋ ግ
ዛቶች ውስጥ፡ማለት በኤርትራ የሰሜን፡የምእራብና የምሥ
ራቅ ረባዳ ክፍሎች ውስጥ ነው፡፡በዳህላቅ ደሴቶችና ከ
ኤርትራም ወሰን በስተሰሜን በሱዳን ውስጥ ቶካራ እስከ
ተባለው ከተማ አካባቢ ድረስ ይነገራል፡፡

/3/ ትግርኛ /ትግራይ/ ቋንቋ፡፡ ተናጋሪዎቹ
ራሳቸውን ትግራይ፡ቋንቋቸውን ትግርኛ በሚል ስም ይጠራ
ሉ፡፡በሌላው ሕዝብ ዘንድ ትግሬ በሚል ስም ይታወቃሉ፡፡
ቋንቋው የሚነገርበት ሥፍራ በኤርትራ ውስጥ በሀማሴን፡
በሠራዬና በገሚስ አከለጉዛይ፡እንዲሁም በትግሬ ጠቅላይ
ግዛት በሙሉ /ከራያና አዘቦ፡እንዲሁም ከአገው ተናጋሪ
ዎች አገር በስተቀር/፡፡በራያና አዘቦም ቢሆን ቋንቋው
ይታወቃል፡፡

/4/ አማርኛ ቋንቋ፡፡ ተናጋሪዎቹ ራሳቸውን አ
ማራ ቋንቋቸውንም አማርኛ በሚል ስም ይጠራሉ፡፡ ቋንቋው
የሚነገርበት ሥፍራ፡— አማርኛ እንደሕዝብ ቋንቋ በሸዋ
ጠቅላይግዛት ገሚስ፡በወሎ ጠቅላይግዛት ገሚስ፡እንዲሁም
በቤገምድርና ጎጃም ጠቅላይግዛቶች ውስጥ ባብዛኛው ቦታ
ይነገራል፡፡ከዚህም በላይ አማርኛ የኢትዮጵያ መንግሥት
ቋንቋ እንደመሆኑ መጠን በየቦታው በትምህርት ቤት፡ባስ
ተዳደር ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች ይሠራበታል፡፡

/5/ አደርኛ ቋንቋ፡፡ባእዱ ጸሀፊዎች ሐረሪ
ይሉታል፡፡ ተናጋሪዎቹ አደሬ፤ የሚነገርበት ሐረር ከተማ



/6/ አርጎባ ቋንቋ፡፡ የሚነገረው በሁለት በጣ
ም በተራራቁ ሥፍራዎች ነው፡፡ የሰሜን ክፍል አርጎባ የ
ሚነገረው በይፋት ውስጥ ሲሆን፡ የደቡብ ክፍል ደግሞ ከ
ሐረር በስተደቡብ በሚገኙ ጥቂት መንደሮች ውስጥ ነው፡፡
አርጎባ በይፋት ለአማርኛ፡በሐረር ለኦሮምኛ ቦታ እየለ
ቀቀ በመሄድ ላይ ነው፡፡

/7/ ጉራግኛ ዘይቤያተለሣን፡፡ ተናጋሪዎቹ ራሳ
ቸውም ሆኑ በሌላው ሕዝብ ዘንድ ጉራጌ በሚል ስም ይጠ
ራሉ፡፡ የሚነገርበት ሥፍራ በሸዋና አሩሲ ጠቅላይግዛቶች
ውስጥ ካዲስአበባ በስተደቡብ፡ከአባያ ሀይቅ የሰሜን ጫ
ፍ እንስቶ እስከጊቤ ወንዝ አጋማሽ ድረስ ባለው ሥፍራ
ነው፡፡ የጉራግኛ ልዩልዩ ዘይቤያተለሣናት ተናጋሪዎች በ
ሙሉ አይግባቡም፡፡እነዚህ ዘይቤዎች እንደሚከተለው በም
እራብ፡በምሥራቅና በሰሜን ቡድኖች ይመደባሉ፡—

ምሥራቃዊ፡—ስልጤ፡ወለኔ /ወለኔ/፡ኡልባረግ /
ኡርባርግ/፡እነቆር፡ዘዋይ—በዝዋይ
ሀይቅ ደሴቶች በሚኖሩ ዓሣአጥማጆች
የሚነገር

ምእራባዊ፡—ቸሃ፡ለግጥም የሚያገለግል ዘይቤ፡
ኤዣ፡ከቸሃ ጋር ይቀራረባል፡ግዬታ
/ጊዬታ/በየሠሪት አካባቢ የሚነገር፡
እነሞር፡ ተናጋሪዎቹ ኢኖር ይሉታል፡
እንደጋኝ፡ ተናጋሪዎቹ ኤንዳገኚ ይሉ
ታል፡፡ሙሁር፡መስቃን፡ጉጉት፡፡

ሰሜናዊ፡— አይመለል፡ለተናጋሪዎቹ አይማላል፡፡

/8/ ጋፋት:: ይህ ቋንቋ ስለከቀርበ ጊዜ ዴረ ስ በጎጃም ጠቅላይግዛት ውስጥ በአባይ ዳር ቻ ሲነገር ስ ነበር:: አሁን ቋንቋውን የሚያውቁ በጁ ጣት የሚቆጠሩ ስ ዎች ብቻ ናቸው:: በቦታው አማርኛ ይነገራል::

---

ማስታወሻ

በጽሁፉ መጨረሻ ደራሲው የሰጠውን የቋንቋዎች ሠ ንጠረዥ ለማውጣት ባለመቻላችን እናዝናለን:: የቴክኒክ ችግር ስላጋጠመን ነው::

አዘጋጅ ቦርዱ::

---

## የመጽሐፍት ዝርዝር


1. Ferguson, Charles A. :"The Ethiopian Language Area". Journal of Ethiopian Studies, Vol.VIII, No.2, July 1970
2. Greenberg, J.H.: "Languages of Africa", Mouton & Co., The Hague, Netherlands, 2nd revised ed. 1966. First pub.1963
3. Jensen, E.(ed.):"Altvölker Süd Äthiopiens" Band I, W. Kohlhammer, Stuttgart,1959
4. Tucker, A.N. and Bryan, M.A. :"Linguistic Analysis of the Non-Bantu Languages of North East Africa". IAI, London,1966
5. Ibid. "The Non-Bantu Languages of North Eastern Africa", IAI, Oxford University Press, London, 1956 .